# ***<u>ወያኔ ማነው?</u>***

***<u>የግል አስተያየት፦ በአያል ሰው ደሴ</u>***

*ብዙ ወገኖች ገና ይኸንን ርዕስ ሲመለከቱ በማፌዝ፣ አልፎም በቅሬታና በቁጣ መንፈስ "ይኼ ደግሞ የማነው እስካሁን የወያኔ ማንነት ያልገባውና ያልተረዳ" አልፎም "የአደባባዩን በጆሮ ሊነግር የሚፈልግ አደናጋሪ!"፣ ለማለት የሚቃጣቸው ወገኖች እንደማይጠፉ እገምታለሁ።*

*ይኸንን ጥያቄ የማነሣው ያለ-ምክንያት አይደለም። መቸም በሕዝባችን ላይ የተጫነውን አምባ-ገነናዊ የአገዛዝ ሥርዓት በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ለመቀየር የማይመኝ ኢትዮጵያዊ የለም። በአብዛኛው ለለውጥ የቆመ ኃይል መኻል በአገራችን ላይ ያለውን አስከፊና አሳሳቢ ሁኔታ በመቀየሩ አስፈላጊነት ረገድ ብዙ ክርክር የሌለ ሊመስል ይችላል። 'ብዙ' ያልኩበትን ምክንያት ግልፅ ላድርግ፡፡ የአገራችንን አንድነትና የሕዝባችንን ሉዓላዊነት የተፈታተኑ ሁኔታዎችን ለመቀየር አሥራ-ስምንት ዓመታት በዘለቀው የወያኔ እና ከሱ በፊት በነበረው ደርጋዊ የአገዛዝ ሥርዓቶች ላይ በተደረጉ የተናጠልም ሆነ የጋራ ትግል ሙከራዎች ውስጥ ቀጥተኛ ተሣታፊ ስለሆንኩ፣ ለለውጥ የቆመው የአንድነት ኃይል አጥጋቢ ውጤት ሊያስመዘግብ ያልቻለበት አንደኛው ዓይነታ ምክንያት የአገዛዙን ባኅሪ በተገቢና በቅጡ ካለመረዳት መሆኑን ስለማምንበት ነው።*

*ማንኛውም ዓይነት ትግል (ፍልሚያ) አዎንታዊና አመርቂ ውጤት ሊኖረው የሚችለው የሚታገለውን (ተፃራሪውን) ክፍል ጠንቅቆ መረዳት ሲቻል ብቻ ነው። የሚደረገውን የትግል ዓይነትና ባኅሪ፣ ዘዴና መንገድ በትክክል ለመወሰንና ለመተለም ይቻል ዘንድ አንፃር ሆኖ የቆመውን ክፍል አጠቃላይ <u>ፍልሥፍናውን፣ አሠራሩንና በግልፅ የሚታዩ ባኅሪያቱን ብቻ ሣይሆን ለባኅሪያቱ መሠረት የሆነውን አስተሳሰብ (ፖለቲካዊ እምነት)፣ የድርጅታዊ ውልደቱን (የአፈጣጠሩን) መሠረታዊ ምክንያት፣ በጊዜው ያለውን (በሥልጣን ላይ ለመቆየት ያስቻለውን) የመኖሪያ መሠረት፣</u> ወዘተ.. በጥንቃቄ ማጥናት፣ በተገቢ ማወቅና መረዳት የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ይኸ ሣይሆን የሚገኝ ድል በራሱ በድርጅቱ ድክመትና የውስጥ ችግር ምክንያት ብቻ በአጋጣሚ የሚገኝ ከመሆን ስለማያልፍ አስተማማኝነት፣ ዘለቄታዊነትም ሆነ ቋሚነት ሊኖረው ያዳግታል።*

## *ለመሆኑ ወያኔ ማነው፣ ምንድነው?*

*ለበርካታ ወገኖቻችን ወያኔ ማለት በጥሬው፣ በተራውና በቀጥታው "የተለመደ" የሚመስለውን "ትርጉም" ማለትም እንደ ስምም ሆነ እንደ ተውላጠ-ስም ትግራይ ክፍለ-አገር ከሚገኘው የአገሪቱ ክፍል የተወለደና ለትግራይ ጥቅም ብቻ የቆመ ሰው፣ እንደተውሳከ-ግሥ ደግሞ ለትግራይ ብቻ መቆምን፣ ፖለቲካዊ ኅጠኛነትንና ኅሠኛነትን እንጂ በቀረው ኢትዮጵያ ለሚኖሩ ዜጎች አለመቆምን የሚገልፅ ተደርጎ ይወሰዳል። ለነገሩ ወያነ (ወያኔ) የሚለው ቃል መወየን/ ወየነ ከሚለው 'ዐበዬ' እንደሚለው እምቢ አለ ወይም አመፀ የሚል ትርጓሜን የያዘ ቃል እንደሆነ ይታመናል። በአንዳንዶች ዘንድ "የመጀመሪያው ወያነ" በሚል የሚታወቀው ንቅናቄ ከጣልያን ወረራ በኋላ አገራዊ ነፃነታችን እንደተመለሰ (ሰንደቅ-ዓላማችን እንደቆመች) ገና መሉ በሙሉ በእግሩ ባልቆመው የአፄ ኃይለ-ሥላሴ መንግሥት ላይ በተለይም እራያና አዘቦን አጣቅሶ ባለው ሕዝብ የተደረገውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ነው። ያ እንቅስቃሴ ልዩ ልዩ አግባባዊ ብሶቶችን የተመረኮዘ መሆኑ ባይካድም ከጀርባው የውጭ ኃይሎች ስውር ደባና መሰሪያዊ ቀስቃሽነት እንደነበረበት ይታወቃል።*

በአሁኑ ጊዜ በሥልጣን ላይ የሚገኘው “የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት” ወያነ (ወያኔ) የምትለዋን ቃል ዘግይቶ በድርጅቱ መጠሪያ ውስጥ የሰነቀረበት የራሱ የሆነ ምክንያት እንዳለው ይነገራል፡፡ አንድም የድርጅቱ አመራር በተወሰኑ የትግራይ አካባቢ (በዋናነት በአድዋ) ተወላጆች በመያዙ በሌሎች ዘንድ ቅሬታዎችን አሣድሮ እንደነበርና በተለይ በደቡባዊና ደቡባዊ-ምሥራቅ የትግራይ አካባቢዎች ተቀባይነትን ለማግኘትና እንቅስቃሴው “ሕዝባዊ” ባኅሪ እንዳለው ለማሳየት ቀደም ሲል ከነበረው የወያነ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጋር ለማዛመድና “ታሪካዊ ትሥሥርና ቀጣይነት” ያለው ትግል እንደሆነ ለማሳየት በስሌት የተደረገ ሙከራ እንደሆነ ይገመታል፡፡

በአንደኛው የዓለም ጦርነት ሣቢያ በአሥራ-አንደኛው ሠዓት፣ በአሥራ-አንደኛው ቀን፣ በአሥራ-አንደኛው ወር በአሥራ-አንድ ዓ/ም (1911)፣ ቨርሣይ (ፈረንሣይ) የተፈረመውን ውል ተከትሎ በጀርመን ላይ በወደቀው ቀጪ አጠቃላይ እቀባ ምክንያት በተከሰተው ቀውስ የጀርመን ሕዝብ ለከፍተኛ ችግር መዳረጉ ይታወቃል፡፡ የጀርመንን ሕዝብ ከደረሰበት ቅጥ-ያጣ የኑሮ ውድነትና ውርደት ለማውጣት በማሰብ በአገር-ወዳድ ጀርመኖች የተደረገውና ከግራም ከቀኝም የፖለቲካ ፍልሥፍናዎችን አጣቅሶ የተነሣው፣ በተግባር ግን አክራሪ የቀኝ ተስፈንጣሪ የሆነው የናዚዎች እንቅስቃሴ የሕዝብ ድጋፍ እንደነበረው ይነገራል፡፡ በሕዝብ ድጋፍም ይኸ በአዶልፍ ሂትለር የተመራው እንቅስቃሴ ወደ ፓርቲነት አድጎ የጀርመን ሠራተኞች ብሔራዊ ሾሻሊስት ፓርቲ (የጀርመን ብሔራዊ ሶሻሊዝም) በመባል ሥልጣን መያዝና የአገሪቱን መንግሥታዊ መዋቅሮች ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ችሏል፡፡ ሆኖም ያ ጀርመንን ብቻ ያስቀደመና “እነሱንና ሌላውን” በጠላትነት ያሰለፈ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ የአገዛዝ ፍልሥፍና መጨረሻው ወደ ጭፍን ጥላቻና ዘረኝነት አድጎ እነሱ “ንፁህ ዘር” ባላሉት ላይ ምን ያኽል ጭካኔ የተሞላበትና ዘግናኝ ኢ-ሰብዓዊ ግፍ የተፈፀመበት ሂደት እንደተስተዋለና ናዚያዊ ፍልሥፍና (ናዚዝም) የጭካኔ፣ የአረመኔነትና የጥላቻ መግለጫ ሆኖ እንዲታይና ስለሆነም የተወገዘ እምነት እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በጣልያን አገር ጣልያናውያንን በአዲስ “ተራማጅ-ብሔረተኛ” እምነት ለመምራት በቤኒቶ ሙሶሎኒ የተመራውና እራሳቸውን የጣልያን ፋሽስት ፓርቲ ብለው በሰየሙ ዜጎች የተደረገው ጭፍን አክራሪና ተስፈንጣሪ የብሔረተኛ እንቅስቃሴ ጣልያንን ለጊዜው “ከሰለጠኑት” አገሮች ጎራ ያሰለፈና የጣልያንን “ክብርና ዝና” ከፍ እንዳደረገ ተደርጎ በራሳቸው በጣሊያኖች ቢወሰድም፣ አገራቸውን ብቻ ሣይሆን አውሮጳን አልፎ የቀረውን ዓለም ባተራመሰው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ውስጥ የከተተና በተለይም እንደ ኢትዮጵያ/ኤርትራ፣ ሊቢያና ሶማሊያ የመሰሉት አገሮች ደግሞ ከፍተኛ የዘረኝነት ፍልሥፍና ላይ ለተመሠረተ ወረራና እልቂት እንደዳረገ ግልፅ ነው፡፡

በጥቅሉ ሠራተኛውን የኅብረተሰብ ክፍል (መደብ) ጥቅም ያስቀደመና በሱና በመደብ ተባባሪዎቹ (አጋሮቹ) ፍፁም የበላይነት (አምባ-ገነንነት) የሚመራ መንግሥታዊ ሥርዓትን ለማስፈን በማርክስና ኤንግልስ ተቀንቅኖ በሂደት እየተለጠጠ በነሌኒን/ስታሊን፣ ማኦ ሴቱንግ፣ ወዘተ.. አዳዲስ አስተሳሰቦችን፣ አዝማሚያዎችን፣ አተረጓጎሞችንና የአፈፃፀም ዘይቤዎችን እየጨመረና እያዘለ ከቦልሸቪኮች ጀምሮ “የኮሚኒስት” እንቅስቃሴ በልዩ ልዩ መልኩ በዓለም ዙሪያ ተካሂዷል፡፡ ይኽንን የፖለቲካ ፍልሥፍና መሠረት አደረግን ብለው በተነሱ ክፍሎች የተዘረጋው ኅብረተሰብን ”በመደብ” ዙሪያ የከፈለ የአገዛዝ ሥርዓትም ዞሮ ዞሮ በሠራተኛው መደብ ስም የተወሰኑ የፓርቲ አባላትን “ልዩና የተመረጡ” ዜጎች አድርጎ ያስቀመጠና አዲስ አናሣ ቁጥር ያለው ጥቅመኛ የኅብረተሰብ ክፍልን የፈጠረ፣ በአንፃሩም የብዙኃኑን መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት የረገጠ የፖለቲካ ዘይቤ ከመሆን እንዳላለፈ በቅርብ የታዬ ክስተት ነው፡፡ ይኸ ደግሞ ይበልጥ “በሦስተኛው ዓለም” ለሚገኙ አፈ-ጮሌ አስመሣዮች ምን ያኽል ሥልጣን ላይ ለመውጣትና ሕዝባቸውን ረግጠው ለመግዛት መጠቀሚያ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ብዙዎች ይኽንን የፖለቲካ ሥርዓት የግፍና ኅብረተሰብን ለችግርና ድህነት የሚዳርግ አድርገው እንዲያዩት አድርጓል፡፡

ከርዕዮታዊ ፍልሥፍና ውጭም እንዲሁ በአንድ አካባቢ ኗሪዎች መካከል በሚገኙ የተወሰኑ ሰዎች አማካይነት የተጀመረ እንቅስቃሴ በዘርም ይሁን በምንም በማይገናኙ በሌላ አካባቢ በሚገኙ የሌሎች አገር ዜጎች ተግባራዊ ሲሆንና ሰዎቹም (ቡድኖቹ) በዚያው ስም መጠቀሳቸውና መታወቂያቸው ሲሆን ተስተውሏል፡፡ ለምሳሌም በጣልያን አገር ችችሊያ (ሲሲሊ) ከምትባለዋ አካባቢ ከሚኖሩ የጣልያን ዜጎች መኻል በአንድ ቤተሰብ አባላት እንደተጀመረ በሚነገርለት የማፍያ ቡድን ስም በየጊዜው የራሽያና የሌሎች አገር ዜጎች የሚያራምዷቸው ከግለሰብ እስከ ጎዋስ ባለ እጅግ የጠበበ ምሥጢራዊ አደረጃጀት የአሠራር ዘይቤን የሚከተል የጥቅም ወንጀለኛ ግለሰቦችም ይሁኑ ቡድኖች "ማፍያ" እየተሰኙ መጠቀሳቸው የተለመደ ነው፡፡

በትውልዱ ሣውዲ አረቢያ እንደሆነ በሚነገርለት ቢን ላደን እንደተጀመረ የሚነገርለትና አል-ቃዒዳ በሚል መጠሪያ የሚታወቀውና ለየት ባለ የአክራሪነት መንፈስ የተደራጀ ድርጅት በዘመናችን "በሐይማኖታዊ" ፍልሥፍና ስም በሚያደርገው እንቅስቃሴ ዓለምን ሲያናውጥ እየተስተዋለ ነው፡፡ በድርጅቱ አክራሪ ፍልሥፍና የተሣቡና ያመኑ በየትኛውም ዓለም የሚኖሩ የልዩ ልዩ አገር ዜጎችም በድርጅቱ በአል-ቃዒዳ ስም በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የየአገሮቻቸው ዜጎችና የእስልምና ሐይማኖት ተከታዮች ላይ ሣይቀር የሚወሰደውን አሳዛኝ እርምጃ እያየን ነው፡፡ የድርጅቱ መሥራች የቢን ላዲን በሕይዎት መኖርና አለመኖር አል-ቃዒዳ እንደ ፍልሥፍና መቀጠልና አለመቀጠሉ ላይ ገዥነት አይኖረውም፡፡ በድርጅቱ ስም የትም የሚደረገው እንቅስቃሴም፣ በአረብ አገር ይደረግ በአውሮጳ፣ በአፍሪቃ ይሁን በሰሜን አሜሪካ፣ በቢን ላዲን ሣይሆን በፍልሥፍናው በአል-ቃዒዳነት ነው የሚታወቀው፡፡

ከዚኽ በላይ የተጠቀሱ ድርጅቶች (በመጠኑ ከናዚዝምና ከፋሽዝም የቀኝ ፅንፈኛ ብሔረተኛ እንቅስቃሴዎች በስተቀር) የርዕዮት ተጋሪነት (ተመሣሣይነት) የላቸውም፡፡ በድርጅታዊ አወቃቀርና በአሠራር ባኅሪያት ግን ይመሣሰላሉ፡፡ የማንኛውም ኮሚኒስት ፓርቲም ሆነ በሱ መልክ በአብዛኛው በስውር አደረጃጀት የሚመሠረትና የሚንቀሳቀስ ድርጅት አባል (ድርጅቱ የፖለቲካ ሥልጣን ይያዝ ወይም በተቃዋሚነት ይሠለፍ)፣ ቅድሚያ ታማኝነቱ ከማንምና ከምንም በፊት ለርዕዮቱ ነው፡፡ አገርም ሆነ ሌላው ከሱ ቀጥሎ የሚመጣ ነው፡፡ እንደ ሕወሓት (ወያኔ) ዓይነቱ በጠባብ **የፖለቲካ ጎጠኝነት**(*1)፣ ያውም "ግራ" ርዕዮትን እከተላለሁ በሚል ጣምራ እምነት ላይ የተመሠረተ ድርጅት አባልም እንዲሁ ሙሉ ታማኝነቱና ታዛዥነቱ ከምንምና ከማንም በላይ ለዚያ ድርጅት ነው፣ ማለት ድርጅቱ ለቆመበት ፍልሥፍና (ፖለቲካዊ እምነት)፡፡

የታጠቀ ጠባብ የፖለቲካ ጎጠኛንም ሆነ አክራሪ ኮሚኒስታዊን፣ ናዚያዊንም ሆነ ፋሽስታዊን፣ አክራሪ "ሐይማኖተኛ"ንም ሆነ እንደ ማፊያ ዓይነት የሥውር ድርጅትን፣ የሚያመሣስሏቸው ባኅርያት አሉ፡፡ በእነዚኽ ፍልሥፍናዎች የሚመሩ ድርጅቶች ከሚያመሣስላቸው አንዱ በአጠቃላይ የሥርዓቶቹ አምባ-ገነናዊ ባኅሪ ብቻ ሣይሆን አንዴ መሪ የተባሉ ግለሰቦችን እስከ ዕለተ-ኅልፈታቸው ድረስ በፍፁም ፈላጭ-ቆራጭነት ማስቀመጣቸው ነው፡፡ ያ ዓይነት ፍልሥፍናን የሚከተል ድርጅት ከዚያ አጥር ውጭ አስፍቶ ለማየትም ሆነ ለመጠየቅ መኖር ያለበትን መሠረታዊ ሰብዓዊ የኅሊና ነፃነት እንዲሁም የአመለካከት አድማስ በእጅጉ ገዳቢ ነው፡፡ ይኽም ስለሆነ የበለጠ ጠባብ የግል ፍላጎታቸውንና የሥልጣን ጥማቸውን ለማርካት መሪዎች የተባሉት ከሚመሩት ድርጅት

**(*1 :-** እዚኽ ላይ "ፖለቲካዊ ጎሠኝነት/ጎጠኝነት" በሚል ያቀረብኩት *በአንድ አገር ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች አካባቢን ወይም ጎሣን መሠረት ባደረገ፣ በሚያቀራርበው ሣይሆን በልዩነት ላይ ያተኮረና አሉታዊነቱ ባመዘነ፣ በ"እኛና እነሱ" መነሻውም መድረሻውም ፖለቲካዊ በሆነ (የትግራይ፣ የአማራ፣ የኦሮሞ፣ ወዘተ... ነፃ-አውጭ) አደረጃጀት እና ገንቢና አዎንታዊ በሆኑ ማኅበራዊ ዓላማዎችና ጉዳዮች ዙሪያ (ለልማት፣ ለመረዳዳትና ልዩ የሆነ ባህልና ልማድን ለማቆየትና ለማዳበር) በሚደረግ አደረጃጀት (የጎንደር ማኅበር፣ የወሎ ማኅበር፣ የጉራጌ ማኅበር፣ ወዘተ..) መኻል ያለውን ግልፅ ልዩነት ለማሣየት ነው፡፡)*

*ውጭ ሕይዎት አለ ብለው የማያስቡ፣ በድርጅቱ ማለትም “በትግሉ”፣ “በርዕዮቱ” ወይም “በአብዮቱ” ስም ሥልጣናቸው የተፈራና የማይደፈር፣ ያለነሱ ቃል ምንም መሆን የማይችልና እነሱ ግን የፈለጉትን ማድረግ የሚቻላቸው ስለሆነ የቅርብ የትግል ጓደኞቻቸውን (ጓዶቻቸውን) ሳይቀር ለማጥፋትና ለማስጠፋት ቅም የማይላቸው ናቸው:: የእነኝኽ ዓይነት ፍልሥፍና መሪዎች እንደ ጆርጂ ኦርዌሉ የእንስሳት እርሻው (አኒማል ፋርም) ናፖሊዮን፣ ሁሉም በጃቸው በደጃቸው የሆነ፣ በሁሉም ረገድ እራሣቸውን ከሁሉምና የሁሉም የበላይ አድርገው የሚያዩና አዲስና ልዩ የበለፀገ ተጠቃሚ መደብ ቁንጮ ሆነው ቁጭ ይላሉ:: እነዚኽ “መሪዎች” እነሱ ቁንጣን ሲይዛቸው ሕዝብ ሁሉ ጠግቦ ያደረ የሚመስላቸው፣ በእነሱ ላይ እስካልተተኮሰ ድረስ እነሱ የፈለጉትን ቢገድሉ አገር ሰላም ነው ብለው የሚያምኑ፣ እኩልነት ማለት እነሱ ከሁሉም በላይ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ የሚመስላቸው፣ እነሱ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሌላው መሰደድ ወይም እስር ቤት መግባቱ አስፈላጊ ሆኖ የሚታያቸው፣ የነሱ መብት የሚረጋገጠው በሌላው (በብዙኃኑ) መብት መጠቅጠቅ የሚመስላቸው ምፀተኛ ፍጡሮች ናቸው:: ይኽ ሁሉ ሲሆን ታዲያ የሚሠራው ሁሉ በአገርና በሕዝብ ስም ነው! አንዳንዶቹም የሚሠሩት ሁሉ ለሕዝብ እንደሆነ እራሣቸውን አሳምነው ነው የሚኳትኑት::*

*ማንኛውም ሰው በእንደዚኽ ዓይነት እምነት ላይ በተመሠረተ ድርጅት ውስጥ አባል ሲሆን በድርጅቱ ስም ምንም ማድረግ ይጠበቅበታል። የእንደዚኽ ዓይነት ድርጅቶች አባላትም አንድ ጊዜ አባል የሆኑበትን ድርጅት አቋም ለምን እንዴት ብሎ መጠየቅ የድርጅቱን (የርዕዮቱን) መሥመር እንደመጠየቅ ወይም በራሱ በድርጅቱ ላይ እምነት እንደሌለ ተደርጎ እንደሚያስቆጥርና ከፍተኛ ነውር ነገር ሆኖ እንዲወሰድ፣ አልፎም የትግል ጓደኞቹንና ዓላማውንም የመክዳት ስሜትን በራስ ላይ እንዲያሳድር የሚያደርግና አመለካከትንም የሚሸብብ ነው:: ይኽም በመሆኑ እራስን አሳልፎ መስጠት ደረጃ የሚያደርስና ሰጥ-ለጥ ብሎ ትዕዛዝ ተቀባይ የሚያደርግ ከባድ ሥነ-ልቦናዊ ጫናን በአባላት ላይ ስለሚያሰፍን፣ ማንኛውም አባል ከላይ የተላለፈን ማንኛውም መልዕክት ያለ አንዳች ጥያቄ መፈፀም ይጠበቅበታል::*

*ይኽን ዓይነት በድርጅት ወይም በትግል ስም የሚቀርብን ማንኛውም ነገር ያለ-ምንም ጥያቄ እንዲፈፅሙ ከአባላት የሚጠይቅና የሚጠብቅ ፍልሥፍና ለጊዜው በአባላት ዘንድ ድርጅታዊ ሥነ-ሥርዓትን ለማስፈን ጠቃሚ ሊሆን የሚችልና ድርጅቱ የቆመበትን የቅርብ ጊዜ ዓላማ እውን ለማድረግ ቢረዳም፣ የድርጅቱ መሪዎች ፈላጭ-ቆራጭ እንዲሆኑና ድርጅቱም ፍፁም አምባ-ገነናዊ እንዲሆን የተመቻቸ ሁኔታን የሚፈጥር ነው:: ድርጅቱ ለመንግሥታዊ ሥልጣን ሲበቃም የድርጅቱ አባላት የሚከተሉትንና የሚፈፅሙትን አጠቃላይ ሕዝቡ እንዲከተልና እንዲፈፅም ድርጅቱ እንደ “ተገቢና መደበኛ” አሠራር አድርጎ ይቆጥራል:: በመሆኑም አመራር የተባለው ክፍል የድርጅቱን አባላት እንደፈለገው እንደሚያዝና የፈለገውንም ያለ ጥያቄ ማድረግ እንደቻለው ሁሉ፣ ያንኑ ያሠራር ልማድ በሕዝብ ላይ ከመጫን ወደ-ኋላ አይልም:: አሁን በአገራችን እየሆነ ያለውም ይኸው ነው::*

*እንደ ወያኔ ወደ ርዕዮት የተለወጠ ፖለቲካዊ ጎጠኝነትም ሆነ በአጠቃላይ ነገሮችን አጥብቦና አክርሮ የሚያይ ፍልሥፍናን የሚከተል ድርጅት አባል መሆን ሚዛኖች ሁሉ አንድ ወጥ እንዲሆኑበትና ሁሉንም በነጭና ጥቁር - “ወይ እኔ ባመንኩት ወይ ጠላት” በሚል አንድ ዓይና መነፅር ማየትን ያስከትላል:: ይኽ ዓይነት ዕይታ ደግሞ በቁሣዊው (ምድራዊ) እምነት ብቻ የተገደበ ሣይሆን እንዲያውም በከፋ መልኩ በሐይማኖት ዙሪያ ያለ አክራሪነት ያስከተለውንና እያደረሰ ያለውን ያስተውሏል:: በአንድ የእምነት ዙሪያ ሣይቀር ክርስቲያን በክርስቲያን (ካቶሊክና ፕሮቴስታንት በአየርላንድ)፣ እስላም በእስላም (ሸዓ እና ሱኒ - እንዲያውም ከዚያም ወርዶ በሸዓም በሱኒም ውስጥ እንኳን “ለዘብተኛ” ናቸው በተባሉት ጭምር) የታየውና የሚታየው አሳዛኝ እልቂት የዚኹ “በእኔ እምነት ካልሆነ” ወይም “እንደኔ ያላመነ ጠላት ነው፤ ጠላት ስለሆነም መጥፋት አለበት” ከሚል ቅጥ-ካጣ የአክራሪነት አስተሳሰብ በመነጨ መንፈስ ነው::*

ብዙ ወገኖች እነ አቶ መለስ የአገሪቱን መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት መዋቅሮችን ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ ቦታዎች “በራሣቸው” ሰዎች ማስያዛቸውን በመገረምም፣ በምሬትና በንዴት ስሜትም ይገልፁታል፡፡ ብዙዎች እንደዚኽ የሚሉ ወገኖች እነሱ በአሁኖቹ ገዥዎች ቦታ ቢሆኑ እንደማያደርጉት ስለሚያውቁ ብቻ አይደለም ያን የሚሉት፡፡ ድርጅቱ (ወያኔ) ከፍተኛ ኃላፊነት የሚጠይቀውን የአገሪቱን የመንግሥትነት ሥልጣን ስለያዘ፣ በያዘው ኃላፊነት መጠንና ከዚያም አኳያ ይሠራል ብለው ከመጠበቅ ነው፡፡ አንድ ብሔራዊ (አገራዊ) የመንግሥትነት ኃላፊነትን የተረከበ ክፍል ዜጎችን ሁሉ በእኩል የኃላፊነት ዓይን አይቶ ያስተዳድራል ከሚል እምነትና ከዚያ ውጭ ይደረጋል ብለው ስለማይጠብቁም ነው፡፡ በበጎ አይተውት ማለት ነው፡፡ ሆኖም እነዚኽ ወገኖች ይኸ ድርጅት (የድርጅቱ መሪዎች) በምን ዓይነት የትግል (የድርጅት) እምነት (ርዕዮት) ውስጥ ተቀርፀው እንዳደጉና ምን ዓይነት ፍልሥፍና እንደሚከተሉ፣ እንዲሁም ሥልጣን ላይ የወጡት ተጠያቂነትን የግድ በሚጠይቀው በሕዝብ ፈቃድና ይሁንታ አለመሆኑን ነው ያላጤኑት፡፡ ይኸ ድርጅት ከትግራይ ወደ ቀረው የአገሪቱ ክፍል ሲሸጋገር፣ ይዞታውን እንጂ መሠረታዊ የሆነውን የፖለቲካ እምነቱን አይደለም የቀየረው፤ ማለትም በተወሰነ አካባቢ (በትግራይ) የነበረውን ይዞታ አስፍቶ በመላ ኢትዮጵያ መዘርጋት መቻሉ ብቻ ነው ልዩነቱ፡፡ ስለሆነም ከ“እነሱና እኛ” ፖለቲካዊ ጎጠኛና ጎሠኛ ጠባብ እምነቱ በመነጨ ፍልሥፍናው መሠረት ሲሠራበት የቆየውን ጠባብና ኢ-ዴሞክራሲያዊ አሠራር ቦታ ስለቀየረ ወይም ይዞታውን ስላሠፋ ሊቀይር አይችልም፡፡

ድርጅቱ ትግራይ ውስጥ ከላይ-እስከ-ታች በዘረጋቸው መዋቅሮች ሁሉ በኃላፊነት ላይ ያስቀመጣቸው በሙሉ ለድርጅቱ እምነት (ርዕዮት) ታማኝ የሆኑ ሰዎችን ብቻ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ይኸ ደግሞ በወያኔ ብቻ ሣይሆን ማንም በዚያ ድርጅት ፍልሥፍና ወይም በተመሣሣይ ጠባብ እምነት የሚመራና ለዚያ ፍልሥፍና ተግባራዊነት የሚጠይቀውን አወቃቀር የያዘ ድርጅት የሚከተለው የአሠራር ዘይቤ ነው፡፡ እስኪ እንመልከት ወያኔ በራሱ ሠራዊት ውስጥ በድርጅቱ ርዕዮት ያልተጠመቀ (ዋና አቀንቃኝ ያልሆነ) ሰው የፈለገውን ያኽል ወታደራዊ እውቀት ቢኖረው በድርጅቱ ወታደራዊ የኃላፊነት ቦታ ላይ ነበር? የማይታሰብ ነው፡፡ ለእንደዚኽ ዓይነት ጠባብ ፍልሥፍና ተከታዮች ዋናው መመዘኛ ድርጅታዊና ርዕዮታዊ ታማኝነት ነው፡፡ ታዲያ ያ የአሠራር ዘይቤ ይዘቱን ሣይቀይር በሂደት ከድርጅት ወደ ትግራይ ሕዝብ ከዚያም በኢትዮጵያ ደረጃ ወደ አጠቃላዩ ነው የሰፋው፡፡

ስለሆነም ይኸ ድርጅት በመላ ኢትዮጵያ ያሉ መንግሥታዊም ሆነ ዋና ዋና መንግሥታዊ ያልሆኑ መዋቅሮችን በራሱ ታማኞች ማስያዙ ሊገርም አይገባም፡፡ በመሠረቱ የዚኽ ድርጅት ፍልሥፍና (“ግራ-ቀመስ” የታጠቀ ጠባብ ፖለቲካዊ ጎጠኛ) ስለሆነ የድርጅቱን አባላት ወደ ቁሣዊነት ባወረደ ደረጃ እንደ ግል (ድርጅታዊ) ንብረቱ እንዲቆጥር ያደረገ እንደሆነ ግልፅ ነው፤ በተግባርም የታየው ይኸው ነው፡፡ በዚኹ “በበላይነት የሚቆጣጠረውን” ክፍል እንደ ግል ንብረት ወይም እንደፈለገው የማድረግ የአስተሳሰብና የአሠራር ልማድ፣ አልፎም እንደማይጠየቅና እንደማይገሠሥ ሙሉ መብቱ አድርጎ በመቁጠር ነው ቀደም ሲል በትግራይ ሕዝብ ላይ ቀጥሎም በቀረው (በመላው) የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያሣየውንና የሚያሣየውን የፈላጭ-ቆራጭነት ባኅሪ ያንፀባረቀውና የሚያንፀባርቀው፡፡

በዚኽ ዓይነት ፍልሥፍና የሚመራና ለዚያም አስተሳሰብ መጣኝ ድርጅታዊ አወቃቀርን የሚከተል ድርጅቶት መሪዎች በተናጠልም ሆነ በቡድን ለሚወስዷቸው ውሳኔዎችና እርምጃዎች በወረቀት ላይ ያለ “ለድርጅቱና ድርጅቱ ለቆመባቸው መርኅዎች ተገዥና ለድርጅቱ ሸንጎ ተጠሪ ናቸው” ከሚል ደፈናዊ አባባል የወጣ ትክክለኛና ተገቢ ተጠያቂነትን ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚይጠይቅና በተጨባጭ ተፈፃሚ የሚያደርግ አስገዳጅነት ያለው አሠራር የላቸውም፡፡ በዚያ የአመራር ክበብ ውስጥ ያሉም አንዱ ሌላውን በዓይነ-ቁራኛ ከመጠበቅና ነገር ትንሽ ወጣ የሚል መስሎ ሲገኝ ለማጥፋት ነቅቶ ከመጠበቅ

ውጭ እርስ-በርስ አንዱ የሌላውን አድራጎት በመሸፈን ይጓዛሉ፡፡ ሁሉም ነገር በድርጅቱና በሚያራምዱት ርዕዮት ስም ስለሚደረግ ለሚወስዱት ማንኛውም እርምጃ ተጠያቂነት የለም፡፡ በዚኽም መንፈስ ነው መሪዎች የተባሉት አጠቃላይ የአገሪቱን ንብረት እንደ ግል ሃብታቸው የሚቆጥሩትና የፈለጋቸውን የሚያደርጉት፡፡ ወያኔም ትላንት በትግራይ ሕዝብ ስም በእርዳታ የተገኘን ገንዘብና ሃብት የግሉ (የአመራሩና የቤተሰቦቻቸው) መበልፀጊያ ሲያደርግ የት አደረስከው ብሎ የጠየቀው የለም፡፡ ለወሰዳቸው እርምጃዎች ሁሉ ተጠያቂነት ኖሮት አያውቅም፡፡ ለምንና እንዴት ተብሎ ሁሉም "ለትግሉና በትግሉ" ስም ነዋ!

እነሱን ሥልጣን ላይ ለማውጣት በተደረገው ትግል ሁሉን ነገር እርግፍ አድርገው ትተው ሕይዎታቸውን ሁሉ ለመስጠት የታገሉ አባሎቻቸውን እነ አቦይ ስብሐት በአንድ ሰዓት ውስጥ ሸረተን ሆቴል ሊያጠፉት ከሚችሉት ያነሰ ገንዘብ እየሰጡ ነው ያሰናበቷቸው፡፡

የአገር ዳር-ድንበርን የሚያኽል ከባድ ጉዳይ ሣይቀር እንኳን ሕዝብ እንዲያውቅና እንዲመክርበት ማድረግ ቀርቶ እንደዚኽ ዓይነት ጉዳዮችን የመወሰን ኃላፊነት ያለው "ፓርላማ" ሣያውቀው ተግባር ላይ ከዋለ በኋላ፣ ያውም "አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ" ወይም ተቃውሞ በይፋ ሲነሣ ብቻ መሆኑ፣ ሕዝብም ጉዱን በግልፅ ማወቅ የሚችለው መንግሥት ነኝ ከሚለው ሣይሆን ነገር ካለቀ በኋላ ከተቃዋሚው ወይም ከመሬት ተረካቢው ክፍል የሚሆነው በዚኹ ድርጅቱ ባደገበትና በሚከተለው ተጠያቂነት-አልባ በሆነው መሠረታዊ ጠባብ ፍልሥፍናው ምክንያት ነው፡፡

ለነገሩ ደርግንም ለውድቀት ከዳረጉት በርካታ ችግሮች መኻል አንደኛው ይኸው በጠባብ ርዕዮት ላይ የተመሠረተ አወቃቀርና አሠራር ነው፡፡ እንደሚታወቀው በየመንግሥት መዋቅሩ እያንዳንዱን የኃላፊነት ጠገግ ተከትሎ የኢሠፓ ታማኝ የፖለቲካ አቀንቃኞችን (ካድሬዎችን) መሰግሰግ የተለመደ ነበር፡፡ በተለይ በሠራዊቱ ደግሞ "የሦስትዮሽ" መዋቅርን ከላይ ጀምሮ እስከ ታች (በአንዳንድ ሁኔታ ሻምበል ደረጃ ድረስ) በመከተል፣ ሠራዊቱን በደንብ የሚያውቁ፣ ብዙ ልምድ ያካበቱ ሞያተኛና በማዕረግም ከፍ ያሉና በዕድሜም የበሰሉ መኰንንኖች የተመደቡበትን ሙያዊ ተልዕኮ በብቃት እንዳይወጡ፣ በተራ-ወታደርና በባለ-ሌላ ማዕረግተኛ የበታች ሹም አፈ-ጮሌ የርዕዮቱ አቀንቃኝና የስለላው መረብ (የደኅንነት) ምጥማጦች ቀጥተኛ ጣልቃ በመግባትና በማያውቁት ወይም ደረጃቸው በማይፈቅድላቸው ወሳኝ ወታደራዊ ጉዳዮች ውስጥ በድንቁርና ድፍረት በሚወስዱት አደናቃፊ እርምጃ፣ አጠቃላይ ተቋማዊ ንቅዘት እንዲሰፍንና ሠራዊነቱንም ለውድቀት እንዳደረሰው ግልፅ ነው፡፡

ለደርግ ግብዝ መሪዎች የታያቸው ሠራዊቱንም ሆነ ሌሎች መንግሥታዊ ዘርፎችን እነሱ እራሳቸው በቅጡ ባልገባቸው አዲስ ርዕዮት "ማነፁ"ና ኅብረተሰቡን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ስለነበር፣ ከችሎታም ሆነ ከሙያዊ ብቃት በላይ በጣም ተፈላጊ የሆነውን ለዚያ ርዕዮትና ለመሪው የማያጠያይቅ ታማኝነት ባላቸው፣ ጥራዝ-ነጠቅ አነብናቢዎችና በብዛት በተመረቱ ግርዶች መሙላቱን ሥራዬ ብለው ተያያዙት፡፡ ያ ዓይነት አሠራር ለአገርና ለሕዝብ መኖር ያለበትን ከፍተኛውን ታማኝነት ሰላቢ ስለሆነ፣ በመጨረሻው "ርዕዮት" የተባለውንም የትውስት ካባ (ድሮም እላይ የተንከራፈፈ ስለነበር) አውልቆ በመጣል፣ ያለ-ምንም ባኅሪው የሌለውን የውደሳ ስም እየተሰጠና በባዶው "ቆራጡ መሪ" እየተባለ የተሞካሸው ኮሎኔልም በችሎታ ማነስና በአረመኔ እርምጃዎቹ ውስጡ እንዲገዘገዝ ያደረገውን ሠራዊት በትኖ፣ አገር ጥሎ ፈረጠጠ፡፡

እዚኽ ላይ ወያኔንና ደርግን ወይም ወያኔንና አንድን በአገራዊ ደረጃ የተደራጀን (ለምሳሌ ኮሚኒስት ፓርቲን)፣ አንደኛው (ወያኔ) እሱ እንደሚለው ለትግራይ የቆመና ሌላው ለመላ አገር የቆመ ሆነው ሳለ እንዴት በእኩልነት ይታያሉ? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡ ሆኖም እዚኽ ላይ በዋናነት መታዬት ያለበት ማን ለማን ቆመ የሚለው ሣይሆን፣ ጫፉ እንደ መርፌ በሾለ ፒራሚዳዊ ቅርፅ ከላይ ወደታች በሚወርድ አወቃቀር የተደራጀና ከማንኛውም አባል ለድርጅቱ አልፎም ኃላፊ (መሪ) ለሆነው ግለሰብ ከማንምና ከምንም በላይ ሙሉ ታዛዥነትንና አመኔታን (መታመንን) የሚጠይቅ ፍልሥፍናን የሚከተሉ መሆናቸውና

ከዚኹ ፍልሥፍናና አወቃቀር በሚመነጭ አምባ-ገነናዊ ባኅሪያቸውና አሠራራቸው ነው:: መመዘንና መታየት ያለባቸውም ከዚኽ አኳያ ነው:: እኔም ለማየት የሞከርኩት ከዚኽና ከዚኽ አንፃር መሆኑ ይታወቅ::

ላለፉት ሰላሣ-አምስት ዓመታት በታየው አውላላ ፖለቲካዊ የፍትጊያ መስክ በአንዱ ወይም በሌላው መሥመር የተሠለፈው ወገን ብዙ ነው:: ወሎዮው "አላህ ሲጣላ በትር አይቆርጥም፣ ያደርጋል እንጂ ነገር እንዳይጥም" እንዳለው አሁን አሁንማ ሌላው የሚናገረውን ሣይሆን እራሱን ብቻ መስማት የሚፈልገው እየበዛ፣ የምፈልገውን እንጂ የተባለውን ማዳመጥና መደማመጥ እያቃተን ስለመጣን እዚኽ ላይ ያቀረብኩን የግል አስተያየት በተመለከተ ሁሉም በየአቅጣጫው እሱን የሚመለከት የሚመስለውን በስንጥር እየመዘዘ "እኔ የታገልኩት ለዚያ ወይም ለዚኽ ድርጅት ብዬ ወይም እከሌን ተከትዬ አልነበረም፣ አይደለምም፣ ስንት ወንድም/እህቶች ውድ ሕይዎታቸውን የገበሩበትንና ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉበትን ትግል እንዴት እንዲኽ ታቃልላለህ፣ ወዘተ.. ድፍረት አይደለም?" አንዳንዱም "እንዴት ነው አገዛዙ የሚያደርጋቸውን አንዳንድ በጎ ነገሮች እንደሌሉ ተደርጎ ሁሉም ነገር በአሉታዊነት የሚታየው?" የሚል እንደሚኖር እገምታለሁ:: ታዲያ ያ አልተግባብቶም! ይሆናል ወገኖቸ:: ነገሮችን፣ በተለይም አገራዊና ሕዝባዊ የሆኑትን፣ ከጥቃቅኑ፣ በየግል ከሚመስለን ወይም ቀደም-ሲል ከያዝነውና እራሣችን ለራሣችን "እውነት" ብለን ከያዝነው ማዕዘን ብቻ ሣይሆን አጠቃላዩን ሥዕልና ሁሉንም ጎን ለማየት እንሞክር::

ስለ ወደፊት የአገራችንና የሕዝባችን እጣ-ፈንታ ከልብ የሚያሳስበው ወገን ሁሉ ዕይታው (ዕይታችን) ወደ-ፊት እንጂ ወደ-ኋላ መሆን የለበትም እላለሁ:: ትግላችን ላለፈው ሣይሆን ለመጭው ትውልዶች መሆን ይኖርበታል:: ወደ-ኋላ ያየ አስተሳሰብ የቂም-በቀልን ጓዝ ከነግትንትሉ ጠቅልሎ የያዘ ስለሆነ ወደ-ፊት እንዳንራመድ ቀይዶ የያዘን ከባድ መሰናክል ነው:: ግልፅ እንሁን፣ ይኽንን አዙሪት እስካልሰበርን ድረስ ደግሞ ምንም ዓይነት የጋራ በጎ ተስፋ አይኖረንም:: እንዴት እከሌን ከገደለ ጋር፣ ይኽንን ካጠፋ ጋር፣ በዚኽን ጊዜ ይኽንን፣ ያንን ካደረገ ጋር፣ ወዘተ... የሚለው አስተሳሰብና አመለካከት ምናልባት ያንን አደረገ የምንለው ሰው ላይ "አግባባዊ" እርምጃ ቢወሰድ መቸም ሰዎች ነንና ለእያንዳንዳችን የግል እርካታን ይሰጠን ይሆናል:: ቁም ነገሩ ግን ያ የተባለው ሰው ደግሞ እኛ እንደተቆጨንላቸው፣ "ደማቸውን እንድንበቀልላቸው" እንደምንፈልግላቸው "የኛዎቹ" ሁሉ ያም ሰው ከእንጨት አልተፈጠረምና የዚያም ሰው "የሱ" የሆኑ "ተቆርቋሪና ደም-መላሽ" "በኛና እኛን" በመሰሉ ወይም እኛን በሚተኩት ላይ በዚያው መንፈስ ያንኑ ከማሰብና ለመፈፀም ከመከጀል ምን ያቆማቸዋል? አዙሪቱ ይቀጥላል ማለት ነው:: ደግሞስ በመኻላችን ያለው ችግር ወይም ልዩነታችን ከየግላችን በላይ በሆነ በአገርና በሕዝብ ጉዳይ ላይ ከሆነ ተፈፀመ የሚባለውን "በደል" ወይም "ወንጀል" በግል (በውልቀ-ሰብ) እንደተደረገ አድርጎ ማየቱ ትክክል ነወይ? ቂምን በግል መቋጠርና ኅሊናችንን ለበቀል ማዘጋጀቱ ወዴት ነው የሚወስደን? ልዩነቱ በአገርና በሕዝብ ጉዳዮች ላይ ሣይሆን በግልም እንኳ ቢሆን በሕግ መዳኘቱ ስለሚሆን ተፈላጊው የሕግ የበላይነትና ፍትኅ የሰፈነበት ሥርዓት እንዲመጣ በጋራ መታገሉ ነው መፍትኄ የሚሆነው:: በአፈ-ታሪክ የሚነገረው በ"ደም መመለስ" የ"ሂሣብ ማወራረድ" ልማድ በሁለቱም በኩል ገዳም የገቡ ሁለት መነኮሣት እስኪቀሩ ድረስ ዘር ሣይተኩ እንደተላለቁት በአንድ አካባቢ የነበሩ ሁለት ቤተሰቦችን አሣዛዥ ሂደት እንከተል ካላልን በስተቀር ይኽ ዓይነት ቅኝት በጥብቅ ሊታሰብበት ይገባል::

ልዩነቶች ለአገርና ለሕዝብ ባሉን መተክሎች ዙሪያ እንጂ በግል እንዳልሆኑ አለመቀበል ከሚፈጥረው የመበቃቀል "ሂሣብ አወራራጅ" ስሊት እራሣችንን ነፃ እስካላደረግን ድረስ አዲስ ሥርዓት፣ አንድነት፣ አብሮ መኖር፣ መቻቻል የሚባሉት ሁሉ ባዶ አባባልና ከንቱ ምኞት ይሆናሉ:: ስለሆነም ቀላል ባይሆንም (መቸም መልካም ሥርዓትን ጨምሮ ጥሩ ነገር ሁሉ በቀላሉ አይገኝም) ለኛ ለየግላችን ሣይሆን ለአንድነታችን፣ ለጋራ ኅልውናችንና ለተሻለ ብሩኅ ተስፋ ካሰብን ያን አዙሪት የመስበር ድፍረቱ ሊኖረን ይገባል እላለሁ:: ይኽንን ደግሞ

ሌሎች ትውልዶች እንዲያደርጉት ባንጠብቅና እራሣችን ያደፈረስነውን እኛው የማጥራት፣ እኛ ያጠርነውን የልዩነት አጥር እኛው የማፍረስ ኃላፊነቱን እኛው ብንወስድ ተገቢ ነው እላለሁ:: ሌላ ማድረግ ባይቻል ቢያንስ ቢያንስ ልዩነትን ለቀጣይ ትውልዶች ማስተላለፍ አይኖርብንም:: እስኪ ማን ጤናማ ወላጅ ነው እያወቀ ለልጆቹ መከራንና ዕዳን ትቶ ማለፍ የሚፈልግ?

**እንደኔ እንደኔ ወደ-ኋላ ሣይሆን የነገን ያየና ኃላፊነት ያለው አካሄድን መከተል የምንችለው በኢሠፓ ይሁን በኢሕአፓ፣ በመኢሶን ይሁን በኢዴኅ፣ በወያኔ ይሁን በኦነግ፣ ወዘተ… በአጠቃላይ በልዩ ልዩ ድርጅት አባልነት፣ በተለያየ መንገድና ዘርፍ በየእምነታቸውና ለየእምነታቸው ተሠልፈው በተለይ ውድና ምትክ የሌለውን አንድ ሕይዎታቸውን አሣልፈው የሰጡም ይሁን በአጠቃላይ የትግል ተሣታፊ የሆኑ ዜጎች ታሪክ የሁላችን የጋራ (የወል) ታሪክ አድርገን መቀበል ስንችል ብቻ ነው::** የወደፊቱ ላይ እናተኩር ካልን ሌላ መንገድ የለም::

አንዳንድ ወገኖች "የኋላውን ያላወቀ ያለፈውን ይደግማል" የሚባለውን አባባል በተዛባ መልኩ የሚወስዱት ይመስለኛል:: ያ ማለትኮ ያለፈውን የሚረሳ የወደፊት ተስፋው የጨገገ ይሆናል፣ የኋላው የወደፊቱን ይገዛል ለማለት ሣይሆን፣ ያለፈው በወደፊቱ ላይ እንቅፋት እንዳይሆን ካለፈው በቂ ትምሕርት እንውሰድ ለማለት እንደሆነ ግልፅ መሆን ያለበት ይመስለኛል::

**እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ደግሞ ውስጡ ላመነበት (በኅሊና አስገዳጅነት) ወይም በልዩ ልዩ ጫናዎችና ግፊቶች ሣቢያ ሌላ አማራጭ በማጣት ተገድዶ እንጂ ማንም ከሞቀ ቤቱ፣ ከሥራ ገበታው፣ ከትምሕርት ቤቱ ብድግ ብሎ ቤተሰቡን በትኖ ጫካ የሚገባም ሆነ ባመቸው መንገድ ለመታገልና ሕይዎቱን አሳልፎ ለመስጠት የሚነሣ የለም:: ስለሆነም የአንዱ አቋም ለሌላችን ይጣመን አይጣመን፣ እንቀበለው አንቀበለው በእምነት የተደረገን አሠላለፍና የተወሰደን አቋም ማክበር ይኖርብናል::** መጥላት ካለብን፣ በተለይ ያ አዙሪት እንዳይደገም ከፈለግን፣ የማንወደውና የማንቀበለውም አቋም እንኳ ቢሆን ብሶት የወለደው ስለሆነ ብሶቱን መረዳትና ቀጣይ ትውልዶች እኛ በተጓዝንበት የጥላቻና የመጠፋፋት ጎዳና እንዳይሄዱ ማድረግ ያስፈልጋል:: እናክብር ማለት ደግሞ እንቀበለው፣ ትክክል ነበር ወይም እንመንበት ማለት አይደለም:: የወያኔንንም ሆነ እሱን መሰል አቋም የሚያራምዱ ክፍሎችን ስለጠላሁ መጀመሪያውኑ እነሱን የፈጠረውን ሁኔታ አላስቀረውም:: መነሻ የሆነውን ምክንያት ነው መጥላትም ማስወገድም የሚኖርብን:: ያ ካልሆነ ለጊዜው ጥያቄውን ያነሱ ክፍሎችን በአንድ መልኩ ወይም በሌላ ማስወገድ ቢቻልም እንኳ ጥያቄው በአጥጋቢ ሁኔታ እስካልተመለሰ ድረስ ለጊዜው ይዳፈን ይሆናል እንጂ ጨርሶ አይጠፋም፣ እስከወዲያኛው ይኖራል:: በተለይም ጥያቄው ፖለቲካዊ ይዘት ካለው አቅጣጫውን ከመቀየሩና ወደ ተካረረና መመለሻ ወደሌለው ደረጃ ከመሸጋገሩ በፊት ፖለቲካዊና ሰላማዊ መፍትሔ ሊገኝለት ይገባል:: ይኽን ለማድረግ ደግሞ የመጀመሪያው እርምጃ ጥያቄው ላይ ችግር ሊኖር ቢችልም ወይም የማንቀበለው ቢሆንም ጥያቄ ያነሳውን ክፍል (ወገን) ግን በአክብሮትና በወገናዊ ስሜትና መንፈስ ማስተናገድ ሲቻል እንጂ በንቀትም ይሁን በማንኳሰስ ወይም በጥላቻ ሊሆን አይገባም::

ግልፅ ለማድረግ ያኽል በዚኽ አጭር ፅሑፍ ለመግለፅ የሞከርኩት በተጠቀሱት ድርጅቶች ውስጥ አባል ሆነው ስለታገሉትም ሆነ ሕይዎታቸውን ስለሰጡ ወገኖች ሣይሆን ድርጅቶቹ ስለተከተሉት/ስለሚከተሉት ፍልሥፍና ነው:: ማንም ቢሆን በዚያ ፍልሥፍና በሚያምን ድርጅት ውስጥ አባል የሆነ ሰው (እኔም ጭምር) የዚኹ መሥመር ተከታይና ዓላማ አስፈፃሚ መሆን እንደሚችል እራስን በነዚያ ሰዎች ቦታ አስቀምጦ ማየት ያስፈልጋል:: ነገሮችን ማገናዘብ በወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ መሠረት ነው::

ደግሞም እስከሚገባኝ ድረስ "እኔ ሞቸ ቀጣዩ ትውልድ ይለፍለት" በሚል እራስን አሣልፎ በሰጠ ቀና አስተሳሰብና እምነት እንጂ እሾማለሁ፣ እሸለማለሁ ብሎ ወይም ሃብታም

ለመሆን አስልቶ የታገለ የለም:: እርግጠኛ ነኝ በሕወሓት ውስጥ ሲታገሉ ውድ ሕይዎታቸውን አሣልፈው የሰጡ ወገኖች፣ ገበሬው፣ የገበሬው ልጅ፣ ተማሪው፣ አስተማሪው፣ ወጣቱ፣ ሴቱ፣ ወንዱ፣ ትልቁ፣ ትንሹ ሁሉ የታገሉት ኤርትራ እንድትገነጠልም ሆነ ድርጅታቸው ኢትዮጵያንና መላ ኢትዮጵያውያንን በፍፁም አምባ-ገነናዊና ዘረኛ አገዛዝ ሥር እንዲወድቁ አስበው አልነበረም:: አይ፣ ሙት አይጠየቅ መቸም!

ስለዚኽ አሁን ይኽ ገዥ ክፍል (ወያኔ) በጠባብ እምነቱ ጠባብ አካሄድን መከተሉ አዲስ ነገር ሆኖ ሊታይ አይገባውም፣ ሊጠበቅ የሚገባው ነገር ነው:: ምናልባት ወደ-ኋላ ማየት ይሆንብኛል እንጂ የዚኽን ድርጅት ፍልሥፍና (ጠባብ ጎጠኛ ርዕዮት) ገና ከጠዋቱ የተቃወሙ ብዙዎች ነበሩ:: ተቃውሞአቸው በጦር መወጋትን ነው ያስከተለባቸው:: ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ገበሬ፣ ተማሪ፣ አስተማሪ፣ ወታደር፣ ወዘተ... የትግራይ ተወላጆች፣ በድርጅት ደረጃ ኢዴኅና ኢሕአፓ ይኽንን ጠባብ ጎጠኛ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ከይሲ ቅኝት ከጅምሩ ተቃውመውታል፣ ተዋግተውታል፣ ከፍተኛ መስዋዕትነትም ከፍለውበታል::

እንግዲኽ የራሽያ ተወላጅ ይሁን የቻይና፣ የአሜሪካ ዜጋ ይሁን የሕንድ፣ አፍሪካዊ ይሁን ካናዳዊ፤ እምነቱና ተግባሩ ፅንፈኛ (አሸባሪ)፣ ፅንፈኛ ቀኝ ይሁን ኮሚዩኒስት ወይም ማፍያ፣ በአገር ደረጃ ለሥልጣን የበቃ ቡድንም እንዲሁ በሚከተለው ፍልሥፍና (ርዕዮት)፣ በሚያራምደው መርኃ-እቅድ (ፖሊሲ) እና መርኃ-ግብር (ፕሮግራም) እንዲሁም በሚያሳየው አጠቃላይ ባኅሪ፣ ከበርቴም ሆነ ፋሽስት፣ ኮሚዩኒስትም ሆነ ፅዮናዊ፣ አፓርታይዳዊም ሆነ ዴሞክራሲያዊ፣ ወዘተ.. የሚሉትን የሥርዓት መግለጫዎች ይላበሳል:: ፅንፈኛ አሸባሪ ሁሉ አረብ፣ ማፍያ ወይም ፋሽስት ሁሉ ጣሊያናዊ፣ የአፓርታይድ ፖሊሲ አራማጅ ሁሉ አፍሪካነር እንዳልሆነ ሁሉ፣ በኔ እምነት ወያኔም ሆነ ወያኔነት በአሁኑ ጊዜ ትግሬነት ቀርቶ የአንድ ድርጅት (የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ) ከመሆን አልፏል::

በእርግጥ ወያኔ (ድርጅቱ) ይኽንን ቃል (ወያነ/ወያኔ) ከትግራይ ሕዝብ ጋር ተጣብቆ እንዲታይ ይፈልጋል:: ምክንያቱም ግልፅ ነው:: ያም በዚኽ ስም የትግራይን ሠፊ ሕዝብ መደበቂያ ለማድረግ ስለሚፈልግ ነው:: በዚኽም ምክንያት የትግራይን ሠፊ ሕዝብ እስረኛው አድርጎ መቀጠል ይፈልጋል:: እግዚአብሄር ያሳያችሁ፣ ይኽ ድርጅት ሠራሁ ያላቸውን ጥሩ ሥራዎች ድርጅቴ ይኽንን አደረገ ነው እንጂ አንድም ቀን የትግራይ ሕዝብ ሠራው ሲል ተሰምቶ አይታወቅም:: እሱ (ድርጅቱም ሆነ መሪዎቹ) በአርገና በሕዝብ ላይ በሚያደርሱት ጥፋት ሲጠየቁ ግን ቶሎ ብለው ድርጅቱ (መሪዎቹ) ላይ ጥያቄ የሚቀርበው የትግራይ ተወላጅ እንደሆኑ አድርጎ ለማቅረብና ያንን ሐጢኣት ወደ ትግራይ ሕዝብ ሊያሸጋግር ይሞክራል:: ይኽ መሰሪነት መቆም አለበት:: ሠፊው የትግራይ ሕዝብን ይኽንን እኩይ ሴራ ሊረዳው ይገባል::

በአሁኑ ጊዜ ወያኔነት ከማንነት መታወቂያነት ይልቅ የምንነት መታወቂያ መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባል:: ስለሆነም ወያኔም ሆነ ወያኔነት ከትግራይ መወለድንም ሆነ ትግሬትን የሚያመለክት ወይም ለትግራይ ክፍለ-አገር ተወላጆች ብቻ የተሰጠ መታወቂያም ሆነ መጠሪያ ተደርጎ መወሰድ አይኖርበትም:: በዚኽ ረገድ ከአሁን በኋላ ማንም ኢትዮጵያዊ ወያኔአዊ ባኅሪያትን ሲገልጽም ሆነ ሲኮንን ማንኛውም የትግራይ ተወላጅ ያ አባባልና አገላለፅ ትግራይንም ሆነ ታላቁን የትግራይ ሕዝብ እንደሚመለከትም ሆነ በነሱ ላይ የተሰነዘረ አድርጎ መውሰድ አይኖርበትም:: በዚያ መልክ መውሰድ እራሱ የጠባብነት ነፀብራቅ ስለሆነ ወያኔነት ተደርጎ ሊቆጠር ይገባል::

ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ በአክብሮት የምጠይቀው ወያኔ የሚለውን ቃል በምንም ዓይነት ከትግራይም ሆነ ከትግሬነት እንዳናዛምድ ነው:: ማንም ጣልያናዊ በሌላ ሰው የማፊያ ስም ሲጠራ፤ ወይም ማንም የጀርመን ተወላጅ ስለ ናዚ ሲወራ እኔን ማለታችሁ ነው ብሎ ሲቀየምም ሆነ ሲያኮርፍ አይቸም ሰምቸም አላውቅም:: እኛስ ወያኔና ወያኔነት አሁን ያለውን ሥርዓት ባኅርያት መታወቂያና መግለጫ እንጂ ከዚያ ያለፈ እንዳልሆነ ለምንድነው

መቀበል ያቃተን? ይኸንን በንፁህ ኅሊና ለማየት እንደምንችልና በመዝገበ-ቃላችን ውስጥ ወያኔ/ወያኔነት ይኸን ትርጉም ብቻ እንደሚይዝ ተስፋ አደርጋለው። ከአሁን በኋላ ኦሮምኛ ይናገር አማርኛ፣ አፋርኛ ይሁን ጉራግኛ ማንም ሥልጣን ላይ ይውጣ ማን፣ አይበልና የዚኸን አገዛዝ አምባ-ገነናዊ ባኅርያት ከያዘ ወያኔ፣ ሥርዓቱም ወያኔአዊ መባል ይኖርበታል። በኔ እምነት አሁንም ቢሆን በተቃዋሚው ክፍል ያለ ይሁን ከአገዛዙ ጋር የተሠለፈ፣ ወያኔኣዊ ፍልሥፍናን ከተከተለና ወያኔኣዊ ባኅሪይ ካለው ወያኔ ነው።

**ለመሆኑ ወያኔነት ምንድነው?**

ከላይ እንደተጠቀሰው በእኔ እምነት በአሁኑ ጊዜ ወያኔነት የአገዛዝ ፍልሥፍና (ርዕዮት) ነው።

የወያኔነት/ወያኔአዊ ፍልሥፍና ምንድነው? መግለጫዎቹስ ምንድን ናቸው?

የሥርዓቱ መግለጫዎች ከእምነቱ (ከፍልሥፍናው) የመነጩት ባኅሪያቱ ናቸው። ታዲያ የዚኸ ሥርዓት ባኅሪያት ምንድናቸው?

ወያኔነት ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው የአስተሳሰብና የአስተዳደር ወይም የአደረጃጀት ፍልሥፍናዎች (ኮሚዩኒስት - በተለይም ስታሊኒስት-፣ አፓርታይዳዊ፣ ፋሽስታዊ፣ ናዚያዊ፣ ፅዮናዊ፣ ማፍያዊ) መግለጫ ከሆኑ ባኅርያት ውስጥ ዋና ዋናዎቹን አጣቅሶ የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን። ከስታሊኒስቶች፣ ከናዚዎች፣ ከፋሽስቶችና ከአፓርታይድ አራማጆች ዘረኝነትንና ከፋፋይነትን፣ ጭካኔንና አፋኝነትን፣ ምፀትን፣ ማዕከሉ የጠበቀ ከላይ ወደታች የወረደ አፋኝ ድርጅታዊ አወቃቀርና ይዞታን፣ ፍፁም አምባ-ገነንነትንና አስመሣይ ተራማጅነትን፣ እብሪትንና ትዕቢትን፤ ከማፍያ፣ ድብቅ፣ መሰሪ፣ የረቀቀና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሁሉ ይሉኝታ-ቢስ በሆነ ስግብግብነት ሃብት ማካበትን፣ ለዚኸ ዓላማውም በማንኛውም መንገድ በጥቅሙ ላይ የቆሙትንና ለሥልጣኑ ጠር የሆኑትን ወይም እንቅፋት ይሆኑኛል ብሎ ያሰባቸውን (በአንድ ወቅት አብረውት የታገሉትን የቅርብ አጋሮቹን ሳይቀር) በርኅራኄ-ቢስነት ከምድረ-ገፅ ማጥፋትን፣ ወዘተ... የአመራር፣ የአሠራርና የአገዛዝ ፍልሥፍናው አድርጎ የያዘ ነው። ወያኔነት ግን ከነዚኸ ፍልሥፍናዎች ውስጥ የናዚንም ሆነ የፋሽስቶችን ያኸል በአገራዊ አንድነት ክብርና ሉዓላዊነት ላይ ተቆርቋሪነትና የማያጠያይቅ ቀናዒነትም ሆነ የአገር ኤኮኖሚን አገር-አቀፍና አድልዖአዊነት በሌለው መልክ የማሳደግ ባኅሪ ሲኖረው አልታየም።

ወያኔነት ማለት ለአገራዊ አንድነት የማይገደው፣ አገራዊ ኃላፊነትን ያለ ብሔራዊ ስሜት የያዘና የአገር ዳር-ድንበርን ለባዕዳን አሣልፎ የሚሰጥ፣ ፀረ-አንድነት፣ ስለ ዜጎች ሰብዓዊ መብት ደንታ የሌለው፣ ሕዝብን ከፋፋይ፣ ተጠያቂነትና ኃላፊነት የሌለው፣ ከአጠቃላይ አገራዊና ሕዝባዊ ጥቅም ይልቅ እጅግ ጠባብ የቡድነኝነት ስሜት የሚያጠቃው፣ ግልፅነት የጎደለውና ድብቅ፣ ሲበዛ ስግብግብ፣ ለሕዝብና ለታሪክ ከበሬታ የሌለው፣ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ምንም ነገር ከማድረግ የማይመለስ (ሌላው ቀርቶ ሥልጣን ከሚለቅ የአክሱም ሐውልት መፍረስን ከመምረጥ ወደ-ኋላ ሊል የማይችል)፣ ሥልጣን የሕዝብ እንደሆነና በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሕዝብ ፈቃደኝነትን እንደሚጠይቅ በተግባር የማይቀበል፣ ሥልጣንን በይገባኛል ብቻ የሙጥኝ የሚል፣ ስለሆነም ሥልጣን ላይ መቀመጥ ከሚጠይቀው ኃላፊነትና ተጠያቂነት ጋር የማይተዋወቅ፣ ጥላቻን፣ አለመቻቻልና ልዩነት ላይ ማተኮርን የሚወድ፣ አስፍቶ ማየትን፣ አገርና ሕዝብን ማስቀደምንና ስለ ነገው ማሰብን፣ መተባበርን፣ የተሠራ ስህተትን መቀበልና ኃላፊነት መውሰድን የሚጠላና የሚፈራ፣ የአስተሳሰብና የአመለካከት ልዩነቶችን በሰላም ማስተናገድና በውይይት መፍታትን፣ ወዘተ.. የማይቀበል ባኅሪው ያደረገ ሥርዓት ነው።

ወያኔና ወያኔአዊነት መገምገም የሚኖርበት ከአነሣሱ ይዞት ከነበረው ትግራይን ያለ ታላቁ የትግራይ ሕዝብ ፈቃድ ከኢትዮጵያ ገንጥሎ 'የትግራይ ሪፓብሊክ'ን የማቋቋም ህልምም ሆነ ትላንት ይከተለው ከነበረው ፀረ-ኢትዮጵያ አቋምና አልፎም አምርሮ ሲያራምደው ከነበረው ፀረ-አማራ አቋም አንፃር ሣይሆን በታሪክ አጋጣሚ እንደዚያ ያንገፈገፈችውንና ከታሪካዊ ጠላቶቿ ጋር ሣይቀር በማበር አጥብቆ የታገላትን የአገረ-ኢትዮጵያን መንግሥታዊ ሥልጣን ከጨበጠበት ጊዜ አንስቶ በሚከተለው መርኅና በሚያሳየው ባኅሪ መሆን ይኖርበታል፡፡ እንግዲኽ ወያኔም ሆነ ወያኔአዊነት መመዘንም ሆነ መታየት የሚኖርባቸው ከዚኽ አንፃር መሆን አለበት እላለሁ፡፡

ይኽ ድርጅት መንግሥታዊ ሥልጣን ለመያዝም ሆነ ከያዘም በኋላ በሥልጣን ላይ ለመቆየት የድርጅቱ አቅም ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ላያጠያይቅ ይችላል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ትግራይን "ነፃ ማውጣት" ዋነኛና ብቸኛ ዓላማው አድርጎ የተነሣ ድርጅት (ከዚኽም እምነቱ በመነጨ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረትን /ኢዴኅን/ እና ኢሕአፓ/ሠን ኅብረ-ብሔራዊ በመሆናቸውና ታጋዮቻቸውም ከሁሉም የአገሪቱ ክፍል የመጡ በመሆናቸው ብቻ ከትግራይ እንዲወጡ ጦር መምዘዙ ይታወቃል)፣ ወያኔ (ድርጅቱ ሕወሓት) ብቻውን ተከዜን ለመሻገር የሚችልበት አሳማኝ እምነታዊም ሆነ ኅሊናዊ (የሞራል) ምክንያትና ብቃት እንዲሁም ጉልበት ሊኖረው እንደማይችል ግልፅ ነው፡፡ ይታያችሁ "የኔ" የሚለውን "ነፃ አወጣለሁ" የሚል (የጋምቤላ ነፃ-አውጭ፣ ወይ የአማራ ነፃ-አውጭ ወይም የሓድያ ነፃ-አውጭ) ትግራይ ተሻግሮ የትግራይን ሕዝብ እንደፈለግሁ ላድርጋችሁ ሲል! ስሜት ይሰጣል? ትርጉም ይኖረዋል?
ለዚኽም ነው ወያኔ (ድርጅቱ) ተከዜን ለመሻገር አሳማኝ እምነታዊም ሆነ ኅሊናዊ ምክንያትና ብቃት አኖረውም ያልኩት፡፡
እዚኽ ላይ እንዴት? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ በእኔ እምነት ያን ማድረግ የቻለው ጠቅለል ባለ መልኩና በአጭሩ በሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ይመስለኛል፡፡

አንደኛ የሰይድ ባሬ ተስፋፊ አምባ-ገነን አገዛዝ በኢትዮጵያ ላይ ያለውን የመሬት ይገባኛል ዕብሪተኛ አቋሙን ለማስፈፀም "የምዕራብ ሶማሌ ነፃ-አውጭ" እና "ሶማሌ አቦ" በመባል ይታወቁ የነበሩ ድርጅቶችን በማሰልጠንና በመስታጠቅ በአብሪነትና ከሱ ጎንም ተሠልፈው የወረራው አጋዥ አድርጎ እንደተጠቀመውና አገራቸውን ኢትዮጵያን እንደወጉ ሁሉ፣ ሸዓብያም በወያኔ መቋቋም ምክንያት ጦርነቱን ከኤርትራ ወደ ትግራይ ማሸጋሸግ (ማስፋት) እንደረዳው ግልፅ ነው፡፡ ያ ደግሞ ሸዓብያ ለቆመበት የግንጠላ ትግል ምን ያኽል ወሳኝ የሆነ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ እንደሰጠው አያጠያይቅም፡፡ ወያኔም በተራው በሱ እምነት ወይም የሱን ገፀ-ባኅሪያት በተላበሱና አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት የሱን ጠባብ ዓላማ ማስፈፀሚያ መሣሪያ በመሆን በአንድ በኩል የወያኔው ትግል ኢትዮጵያዊ ገፅታ እንዲኖረውና ሕዝብ በተለይም ወታደሩ ጥርጣሬውና ተቃውሞው ረገብ እንዲል በማስቻል፣ በሌላ በኩል በቀዳሚ አብሪነት ብቻ ሣይሆን በጦርነቱም ቀጥተኛ አጋዥ በመሆን ባገለገሉት ወገኖች አማካይነት ጦርነቱን ወደ መኻል አገር ማስፋትና ከኋላው (ከጀርባው) የሸዓብያ ሽፋን ስላለው ትግራይ ውስጥ ያለ-ማንም ጣልቃ-ገብነት ደጀኑን በሚገባ ማሰናዳትና ድርጅቱን ለማጠናከር በመቻሉ፤

ሁለተኛ ደርግ የተባለው አገዛዝ በሚከተላቸው ፀረ-ሕዝብ ፖሊሲዎች ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፉን ስለነሣውና እጅግ ደካማ፣ የአመራር ብቃትና ችሎታ የሌለው ልፍስፍስ በመሆኑ በአገሪቱ ላይ አንፃራዊ ክፍተትን የፈጠረው አመች ሁኔታ፤

ሦስተኛ በድርጅቱ (በወያኔ) ማዕከላዊነትን በጣም ያጠበቀ ወታደራዊ አደረጃጀትና ዓለም-አቀፍ (በተለይ የምዕራቡን ዓለም) ባለ ብዙ ፈርጅ እርዳታና ትብብርን ሊያስገኝነት የቻለ ብልጠት የተሞላበት ቅኝት፤ ናቸው፡፡

*ቀደም ሲል ለማስገንዘብ እንደሞከርኩት በእኔ እምነት በአሁኑ ጊዜ ወያኔና ወያኔነት እንዲሁ በአንድ አካባቢ (በትግራይ) ለተወለዱ ግለሰቦችም ይሁን የነሱ ስብስብ ለሆነው ድርጅት መጠሪያነት ብቻ ሊውል የሚገባበት ጊዜ አክትሟል። ምንም እንኳ ድርጅቱ (ወያኔ) አገራዊ የመንግሥት ሥልጣንን ቢጨብጥም ቅሉ ድርጅቱ በመሠረቱ ለቆመባቸው መርኅዎችና ለሚከተላቸው ፖሊሲዎች ተገዥ ከመሆንና እነዚያ እምነቶችም ድርጅቱ ለሚያራምደው የአገዛዝ ሥርዓት ዋነኛ የመኖር ምክንያትና የኀልውና መሠረት እንደሚሆኑ ሊታወቅ ይገባል።*

*ወያኔ ቆምኩለት ከሚለው ከትግራይ ወደ ቀረው የአገሪቱ ክፍሎች ለመሸጋገር የቻለው ሌሎች ኃይሎችን እንደ መከታና ጭምብል እንደተጠቀመ ሁሉ፣ በትግራይ ሕዝብ ላይ ያሰፈነውን አምባ-ገነናዊ የአገዛዝ ሥርዓቱን በመላ አገሪቱ ለመጫንም ሆነ በሥልጣን ላይ ለመቆየት እንዲሁ ሌሎች በሱ ፍልሥፍና የተገሩና የተጠመቁ የአማራ ወያኔዎችን፣ የኦሮሞ ወያኔዎችን፣ የጉራጌ ወያኔዎችን፣ የጋምቤላ ወያኔዎችን፣ የደቡብ ወያኔዎችን፣ ወዘተ... በአባሪ ተባባሪነት ተጠቅሟል፣ እየተጠቀመም ነው። እግዚአብሔር ያሳያችሁ ያለነዚኽ ኃይሎች ቀጥተኛ አባሪ ተባባሪነትና ተከታይነት ይኽ አገዛዝ ለዚኽን ያኽል ጊዜ በኢትዮጵያ መንግሥትነት መቆየት ሲችል። ለዚኽም ነው ወያኔ ጎሣም ሆነ ጎጥ የማይገድበውና ለአንድ ለትግራይ ወገናችን ብቻ የሚተው ስያሜ ሣይሆን የሥርዓት ዘይቤ ነው የምለው።*

*ከማንኛውም የአገሪቱ ክፍል ይወለድ ከየት ማንኛውም ፀረ-አንድነት፣ ፀረ-ኢትዮጵያዊነት፣ ፀረ-ፍትኅ፣ ፀረ-ዴሞክራሲ፣ ፀረ-መቻቻል፣ አድልዖአዊ፣ ጠባብ፣ ራስ-ወዳድ፣ ቂመኛ፣ ይቅርታን የማያውቅ፣ ፖለቲካዊ ኅጠኛና ኅሠኛ አቋም ያለው፣ ሉዓላዊነት የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን የማይቀበል፣ የሕዝብን ድምፅ የማያከብር፣ ለሕዝብ፣ ለታሪክና ቅርስ አክብሮት የሌለው፣ የሕግ የበላይነትን የማይቀበልና የማያከብር፣ ሥልጣንን ከአገርና ከሕዝብ በላይ የሚያፈቅር (ለሥልጣን የሚስገበገብ)፣ ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር የሚሠለፍ (የሚተባበር)፣ ለጥቅም ያደረ፣ ምንደኛ፣ እብሪተኛ ሁሉ ወያኔ ነው። በእኔ እምነት በአካል ከአገዛዙ ጎን ይሠለፍ ወይም ከተቃዋሚው ጎራ ይሁን፣ የማንኛውም ሰው ወያኔ መሆንና አለመሆን የሚለካው በነዚኽ መመዘኛዎችና በነዚኽ ላይ ባለው አቋም፣ አስተሳሰብና ከነዚኽ አኳያ በተግባር በሚያሣየው ባኅሪው መሆን ይኖርበታል። ወያኔን በትግሬነት መፈረጅ በራሱ ወያኔአዊ አስተሳሰብ ነው።*

*'ወያኔማ ወያኔ ነው ይኽንን ማን ያጣዋል' የሚል ስለማይጠፋ እንደገና ይኽንን በተራው ግልፅ ማድረግ ያስፈልግ ይመስለኛል። አብዛኛው ሰው የአገዛዙን ምንነት የሚወስደው (የሚረዳው) በግልቡ ስለሆነ በድርጅት ደረጃ አልፎም ግለሰቦቹ (መሪዎቹ) ላይ ያንዣበበና ችግሩም መፍትኄ የሚባለውም ሁሉም መነሻውም መድረሻውም በነሱ ላይ የተንጠለጠለ አድርጎ በቁንፅል የማየት ችግር አለ። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በአሁኑ ጊዜ ወያኔነት ትግሬነት የሚመስላቸው ካሉ ተሳስተዋል። ወያኔነት አንዳንዶች እንደሚሉት ሳይሆን ከትግሬነት ቀርቶ ከሕወሓትነት አልፏል። (በግሌ ወያኔ /ድርጅቱ/ እና ሠፊውን የትግራይ ሕዝብ አንድ አድርጌ አላይም፣ አይቼም አላውቅም)።*

*ግልፅ እንሁን፣ ወያኔነት የፍልሥፍና እምነት (ርዕዮት) ነው። የአስተዳደር (የአገዛዝ) ዘይቤ ነው። አስተሳሰብ ነው። አስተሳሰብ እንደ ተስቦ (ወረርሽኝ) ተላላፊ ነው። አልፎም እንደ መርዝ ነው። ተላላፊ በሽታን ወይም መርዝን መዋጋት (መከላከል) ወደ ሰውነት ውስጥ ሣይገባ፣ ከገባም ቶሎ ብሎ የመሰራጨት ዕድል ሣይኖረው ብቻ እንደሆነ ሁሉ አሉታዊ አስተሳሰብም ሳያንሠራራና ሌላውን ሳይበክል እንጂ ከበከለ በኋላ የአሉታዊ አስተሳሰቡ ምንጭ የነበረው ላይ ብቻ ማተኮሩ ወይም እሱን ብቻ በማስወገድ በሽታው እንደሚወገድ አድርጎ መቁጠር የተበከለው ሁሉ ሌላ በካይ እንደሚሆን አለማወቅ ይሆናል። አለበለዚያ ደግሞ የተበከለው ሁሉ ብክላውን (በሽታውን) ለጤነኛ እንዳያስተላልፍ እንዲለይ መደረግ ሊኖርበት ነው። የሚለየውም አንድም ሙሉ በሙሉ ጤነኛ መሆኑና በሽታውን እንደማያስተላልፍ በማረጋገጥ መፍትኄ ሲገኝ ወይም የተበከለው እንዲጠፋ (እንዲከስም)*

ሲደረግ ነው። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የወያኔኣዊ ጎጠኛ አስተሳሰብ (እምነት) በሽታ በብዙዎች ዘንድ ስለተዛመተ የትኛውን መንገድ በመከተል ነው ይኸ በሽታ እንዲከስም (እንዲጠፋ) ማድረግ የሚቻለው? መቸም የተበከለውን ሁሉ በማጥፋት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል። ለምን ቢሉ፤ "ሁሉ በሽተኛ ሁሉ ራሴን ባይ፣ ባገሬ ጤነኛ ላይገኝ ነወይ?" እንዲሉ ሆኗልና።

እስኪ የምር እያንዳንዳችን እራሳችንን እንጠይቅ፣ ስንቶቻችን ነን በሃቅ ከዚኸ ልክፍት ነፃ የሆን? አወቅነውም አላወቅነው፣ አስልተንም ይሁን በምሬት የጎጠኝነት ነቀርሣ በሚያሳዝን መልኩ በኅብረተሰባችን ውስጥ ተዛምቷል። እዚኸ ላይ አንድ ነጠላ ክስተት ልጥቀስ። በሸዓብያ ዕብሪተኞች ጠብ-አጫሪነት ጦርነት በተጀመረበት ጊዜ በአንድ ወቅት ተራማጅ (ያውም ዓለም-አቀፋዊ!) እንደነበር የሚነገርለት "ምሁር" ዋሽንግተን ውስጥ ለአንድ ቀድሞ የኢሕአፓ አባል የነበረና በዘመኑ የጎጠኝነት በሽታ ተለክፎ ወደ አገዛዙ የፖለቲካ መስመር አቀንቃኝነት (ካድሬነት) 'ለተለወጠ' ሰው "በዚኸ ጦርነት ሳቢያ አማሮች እንዳይጠቀሙ (advantage እንዳይወስዱ) ከፍተኛ ትኩረትና ጥንቃቄ ማድረግ አለባችሁ" ሲል ማስጠንቀቂያ-አዘል ምክር ሲሰጥ መደመጡ ይኸ የጎጠኝነት ጠባብ አመለካከትና እምነት ምን ያኸል እንደበከለን ያስረዳል። የሚገርመው ለዚያ በአሜሪካ አገር የዩኒቨርሲቲ መምህር ለሆነ ኢትዮጵያዊ የቀረቀረውና ያሣሰበው ያ ጦርነት ጎሣን፣ ቋንቋንም ይሁን የፖለቲካ እምነትንና ሐይማኖትን ሣይለይ በንፁኃን ዜጎች ላይ የሚያስከትለው እልቂት፣ ሰቆቃና ፍዳም ሆነ በአጠቃላይ በአገራችንና በአካባቢያችን ላይ የሚፈጥረው ቀውስ ሣይሆን ጎጠኝነቱ፣ አጥንት ቆጠራው ነበር! እርግጠኛ ነኝ ይኸን የዞረበትና ጤና-ቢስ አስተሳሰብ ከእንደርታም ይሁን ከአጋመ፣ ከአድዋም ይሁን ከአክሱም፣ ከሽሬም ይሁን ከሁለት አውላሎ ገበሬ አፍ አይወጣም።

የኢትዮጵያ ልሂቃን በዚኸ አሉታዊና ኋላ-ቀር አስተሳሰብና እምነት (ፍልሥፍና) ተመርዘው የየራሳቸውን ፖለቲካዊ የጎሠኝነትና የጎጠኝነት አጥር አጥረው ሕዝባችን ተለያይቶ እንዲያድግ ልባቸው እስኪወልቅ ጥረታቸውን ቀጥለዋል። ዕድሜ ለዚኸ አገዛዝ፣ ልዩነት ላይ ያተኮረና ከፋፋይ ጎጠኛ የፖለቲካ ፍልሥፍናው የአገዛዙ መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲሆን በመደረጉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነት ትሥሥር ገመዱን አልበጥስ ብሎ ታገላቸው እንጂ እንደ እነሱ ቢሆን እስካሁን አገር አንድ ሆና አትቀጥልም ነበር። ሕዝባችን ግን ከመነጣጠል ይልቅ የጋራ ጥቅሙ የተሻለ መከበርና መጠበቅ የሚችለው በአንድነቱ መሆኑን ማመኑ በተግባር እያረጋገጠ ነው።

በሽታው ይበልጥ የጠናው በልሂቃኑ ዘንድ እንደሆነ ግልፅ ነው። እነሆ ሌላው ቀርቶ በድርጅት ደረጃ "በጋራ አገራዊና ሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ አንድ ላይ ለመቆምና በጋራ ለመሥራት (ለመታገል) ተስማምተናል" ብለው የሚያውጁ ድርጅቶች (ያውም በአገሪቱ የፖለቲካ መስክ ረዘም ላለ ጊዜ የቆዩና "እየሰከኑ" መጥተዋል ተብለው በሚታሰቡ ወገኖች)፤ "ወጣ ወጣና እንደ ሽምበቆ ...." እንዲሉ በተለይ "ምርጫ" የሚሉት ኢሕአዴጋዊ ጨዋታ ብቅ ባለ ቁጥር ትላንት የተባለው ሁሉ ይረሳና "በኔ ክልል ሌላው አይገባም... አትድረሱብኝ" የሚለው "ጨዋታ ፈረሰ፣ ዳቦ ተቆረሰ" ዓይነት ቧልት አገርሽቶ ያ በውስጣቸው ሰርፆ ገብቶ ቤቱን አደላድሎ የሠራባቸው የልዩነትና የጎጠኝነት እምነት  ብቅ ሲል ይታላል። ያው አሁንም እንኳ "መድረክ" በተባለው ስብስብ ይኸው ልክፍት እየተንፀባረቀ መሆኑን በትዝብት እየተመለከትን ነው።

አንዳንድ ወገኖች "የትግራይ ነፃ-አውጭ" ድርጅት ይኸውና አሥራ-ስምንት ዓመት ሙሉ በአገራዊ ሥልጣን ላይ ተቀምጦም እንኳ ከጎጠኝነት አስተሳሰብና ስሜት ሊላቀቅ አልቻለም፤ ይኸው የጦር ኃይሉንም ሆነ አጠቃላይ መንግሥታዊ መዋቅሮችን ከላይ እስከታች 'በራሱ ሰዎች' ብቻ ይዟል፣ ወዘተ..." ሲሉ በግሌ በጣም ይገርመኛል። የሚገርመኝ ግን ከሃቁ ጋር ችግር ኖሮኝ አይደለም። ሃቁማ አፍጥጦ አግጥጦ ያለ ሃቅ ነው። ችግሩ ያለው አቤ ኃይለ-ሥላሴ ለምን ኮሚዩኒስት አልሆኑም፣ ወይም ለምን እምቢይ ብርቱካን አልሆነም

ዓይነት ስለሆነብኝ ነው:: እንዴ ይኸ ድርጅት ለምን እንደቆመና እንደታገለ አሥራ-ሰባት ዓመታት ሙሉ በድብቅ ሣይሆን በአደባባይ እየተናገረ! አገራዊ ሥልጣን እንደያዘም ዋና ቀዳሚ ዘመቻው በብሔራዊ (አገራዊ) ተቋማትና ተምሳሌቶች ላይ እንደሆ በተግባር አሣይቶ! ያም ሁሉ እንኳን ሆኖ ይኸ ድርጅት ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምናልባት በሂደት አገራዊ ስሜትና ብሔራዊ ኃላፊነት ይሰማው ይሆናል ብሎ እንዲቀየር በትእግሥት ቢጠብቅና ዕድል ቢሰጠውም ስሙን እንኳን ለመቀየር አልሞከረም:: በአካል ቤተ-መንግሥት ቢሆንም በመንፈስና በውጣዊ እምነቱ አሁንም ደደቢት ነው፣ አሁንም በ"እኝኛ እና እነሱ" መርዘኛ አስተሳሰብ እንደተበከለ ነው:: ለመቀየር ከዚኸ የበለጠ ምን ታላቅ ዕድል ነበር? ግን ሊሆን አልቻለም፣ እንዴት ተደርጎ! በቀላሉ ይሆናል ብሎ ማሰቡም ሲበዛ የዋህነት ነው:: (ድርጅቱ ተከዜን መሻገር በጀመረበትና በቀረው ኢትዮጵያዊ በተለይ ጠንካራ ኢትዮጵያዊ አቋም ያላቸውንና የነሱን (የወያኔን) አቋም ጨርሶ የማይደግፉ የትግራይ ተወላጆችን እየፈለገ ለማሳመንና ደጋፊ ለማድረግ ስለ ኢትዮጵያ ማውራት የጀመረበት ወቅት ላይ፣ በግለጫዎቻችሁ ላይ ይኸን ያኸል "የኢትዮጵያ ወታደር ገደልኩ፣ ማረኩ" የሚለውን ለምን "የመንግሥት ወታደር" አትሉም ተብለው ተጠይቀው "ይታሰብበታል" የሚል መልስ ቢሰጡም ውስጥጣቸው ያላመነበትን ማድረግ ስላልቻሉ መግለጫዎቻቸው በዚያው በተለመደውና ልክ አጋራቸው ሰይድ ባሬ ይል በነበረው መልክ አባባሉን ሣይቀይሩ ማውጣት መቀጠላቸውን አስታውሳለሁ)::

ጥያቄው የግርንቢጥ ይሁን ካልተባለ በስተቀር መሆን ያለበት ለምን ይቀየር? እንዲሁ መቀየርስ ድርጅታዊ ተፈጥሮው ያስችለዋል ወይ? የሚለው ይመስለኛል:: መንግሥታዊ መዋቅሮችን "በራሱ ሰዎች" የሚሞላው አዲስ የማይሆነውኮ መጀመሪያውኑ "በእኛና እነሱ" እምነት የታነፀ አእምሮና በዚያ የልዩነት ፍልሥፍና የሚመራ ሥርዓትን እያራመዱ እንዴት ተደርጎ ነው "እነሱን ያልመሰለውን" ሰው አምነው ሥልጣን የሚያጋሩት ወይም ቁልፍ የኃላፊነት ቦታ ላይ የሚያስቀምጡት? በዚያ ጤና-ቢስ አስተሳሰብ ለተቀረፀ መርጎ "ሌላው" እኮ ለነሱ ባዕድ ነው፤ የትግሉ መሠረት እሱ ነዋ! በኮሚኒስት ፓርቲ የሚመራ ሥርዓት መንግሥታዊ መዋቅሩን የሚያስይዘው "የራሴ" ናቸው በሚላቸው የፓርቲው አባላት (በኮሚኒስቶች)፣ በቀኝ ፅንፈኛ አክራሪዎች የሚመራም እንዲኹ የእሱን መሰል እምነት ባላቸው ሰዎች ብቻ ነው:: ማፍያ የንግድ መሥመሩን ቁጥጥር በሌላው ማፍያ አባሉ እንደሚያስይዝ ማለት ነው:: ግራ ቀኝ የማያሰኝ የእምነት (የርዕዮት) ጉዳይ ነው:: ለዚኸ ነው ሊገርም አይገባም የምለው:: ዞሮ ዞሮ አሁንም ወያኔ ይኸንን የሚያደርገው እነሱ ስለሆኑ (በነሱነታቸው) ሣይሆን የሚከተሉት የ"ነሱና እኛ" ፍልሥፍና የግድ ስለሚል ነው::

እርግጠኛ እንሁን፤ አሁን ይኸ ድርጅት የሚያደርገውን ማንም በዚኸ ድርጅት ፍልሥፍና የሚመራ "ነፃ-አውጭ" ድርጅት ሁሉ በሱ ቦታ ላይ ቢሆን የሚያደርገው ነው:: በድጋሜ ግልፅ ለማድረግ፣ <u>ወያኔ የሚያደርገውን የሚያደርገው በሚከተለው ፍልሥፍና እንጂ ከትግራይ ስለመጣ አይደለም::</u> ይኸንን ነጥብ ነው በተለይ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፈው የአንድነት ኃይል የማያጤነው:: ከጥቂት ወራት በፊት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) 'ይቻላል' በተሰኘው ልሣኑ "የትግራይን ሕዝብ ለቀቅ፣ ወያኔን ጠበቅ" በሚል ርዕስ ያቀረበው ትችት ይኸንን ነጥብ በዝርዝር አስረድቷል:: ስለዚኸ ኢትዮጵያውያን መገንዘብ የሚኖርብን ትኩረታችን የመከፋፈልና የልዩነት ሥርዓት አራማጆች ላይ በቁንፅል ሣይሆን እራሱ "እነሱና እኛ" እምነቱ (ርዕዮቱ) ላይ መሆን ይኖርበታል:: ይኸ ርዕዮት በአሁኑ ጊዜ አዲስ ስም ይዟል፤ ወያኔ/ወያኔኣዊ ተብሏል:: እንደ ደርግ ወይም ማንኛውም ወታደራዊ መንግሥት (ጁንታ) በየትኛውም አገር ባሉ ወታደሮች ይሁን በማን የአገዛዛቸው ሥርዓት ወታደራዊ ደርግ (ጁንታዊ) ነው የሚሆነው::

ስለሆነም ሥርዓቱን ለመቀየር ከተፈለገ መልዕክተኞቹን (አስፈጻሚዎቹን) ብቻ ሣይሆን ዋና ፍልሥፍናውን መመንገል ነው መፍትኄው:: መቆሚያ መሠረቱ ያልተነካበት (ያልተበሳ) ዛፍ አይመነገልም:: መቁረጥ ይቻላል፤ ሆኖም የተቆረጠ መልሶ ማቆጥቆጡ (ያውም ከአንድ በላይ ሆኖ) አይቀርም:: ሥርዓትም እንዲሁ ነው:: አንድን ሥርዓት

መቀየርና አንድን አገዛዝ መቀየር የዛፍ ቅርንጫፍን መከርከምና ዛፍን ከሥሩ (ያውም ሥሩ ሩቅ የሄደን የበረሃ ዛፍ) መንግሎ የመጣልን ያኽል ልዩነት አለው።

እስኪ በተቃዋሚው ጎራ ያለውን አሠላለፍ እንይ። ስንቶቹ ናቸው ከወያኔ ድርጅትና ከመሪዎቹ ጋር እንጂ ከወያኔአዊ አስተሳሰብ (ፍልሥፍና) ጋር ችግር የሌላቸው? በአንድ ወቅት የቤኒሻንጉል "ክልል" ቋንቋ አረብኛ ካልሆነ ብሎ ከወያኔ ዘለቄታዊ የአስተሳሰብ (ስትራቴጂያዊ) አጋሩ ጋር ከተኳረፈው የቤኒሻንጉል "ነፃ-አውጭ" ግንባር ጋር የወያኔን መሠረታዊ ከፋፋይና ጎሠኛ ርዕዮት አጥብቄ እቃወማለሁ የሚል ድርጅት "ግንባር" ፈጠርኩ ብሎ ሲፎክር ተሰተውሏል። አንዳንድ ወገኖች ወያኔን ለማስወገድ ከሱ (ከወያኔ) ጋር ተመሣሣይ እምነት (ፍልሥፍና) ካላቸውም ክፍሎች ጋር ስልታዊ ትብብር ማድረጉ አስፈላጊ ነው፣ ይኸ ምንም ችግር የለበትም ይላሉ። እንዲኸ በሚሉ ወገኖች አስተሳሰብ "ትልቁን ሰይጣን" ለማስወገድ "ከትንንሽ ሰይጣኖች" ጋር ማበርና በተባበር አስፈላጊ ነው ማለት ነው። ለመሆኑ ሰይጣን ትልቅና ትንሽ የሚል ደረጃ አለው? በእውነት አላውቅም። የዚኸ ዓይነት አስተሳሰብ ግን የጠገበ ጅብን ለማባረር የተራቡ ጅቦችን መወዳጀት ዓይነት ስለሚሆን የምር የሚታሰብበት ጉዳይ ነው።

እዚኸ ላይ አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ አለ። ከወያኔ ተመሣሣይ አቋም ያለውን ሁሉ እንዲያው በደፈናው በሩቁ ለማለት ሣይሆን፣ ይኸን አገዛዝ የምንቃወምበት መተከላችን ምንድነው የሚለውን በግልፅ መረዳት ስለሚያስፈልግ ነው። ግልፅ እንሁን፤ በኢትዮጵያ ውስጥ በልዩ ልዩ መልክ የተደራጁ ቡድኖች ከባዶ ተነስተው ወይም "ጠግበው" ወይም ፈልገው ሣይሆን በአገሪቱ ውስጥ በተከሰተው ሁኔታ ምክንያት እንደሆነ ይገነዘቧል። ያለው ነባራዊ ሁኔታ የወለዳቸው ናቸው። ጥያቄአቸው በቀና መንፈስና በተገቢ እንዲስተናገድላቸው ስላስፈለገ ነው። ጥያቄ ያነሣ ሁሉ ያ የተነሣ ጥያቄ የግድ ትክክል ወይም ተገቢ ነው ማለት ግን አይደለም። ቁም ነገሩ ግን ምክንያት-አልባ የሚነሣ ጥያቄ ስለሌለ ጥያቄውን በተገቢና በሰላም ማስተናገዱ ትክክል ብቻ ሣይሆን ያን ባለማድረግ ሳቢያ በአገር ላይና በተለይም ጥያቄው በስሙ በተነሣበት ሕዝብ መኻል ንፁኃኑ ላይ የሚያስከትለውን የባሰ ችግር ማስወገድ ስለሚያስችል ጭምር ነው።

የወያኔን ማንነትና ምንነት እንረዳ የምለው ለአንድነት፣ ለፍትኅ፣ ለእኩልነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን የምንታገል ወገኖች ይኸንን የአገዛዝ ሥርዓት የምንቃወምበትን መሠረታዊ ምክንያት በግልፅ ማወቅ ይገባል ብየ ስለማምን ነው። ከዚኸ መሠራዊ አቋም በመነሣት ነው አሁን ያለውን "ሕገ-መንግሥት" በቅርብ መፈተሹ አስፈላጊ ነው የምንለው። አንዳንድ ወገኖች የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት ገና ሲረቀቅ ጀምሮ መሠረታዊ ችግር አለው የምንለው ይኸንን መሰል አምባ-ገነናዊ ሥርዓትን አቅፎ-ደግፎ የሚይዝ ስለሆነ ነው። በምርጫ ዘጠና-ሰባት አካባቢ ይኸ ጉዳይ ምን ያኽል አወዛጋቢ እንደነበር ይታወቃል። "ከአገዛዙ እንጂ ከሕገ-መንግሥቱ ጋር ችግር የለንም" የሚሉና አገዛዙን እንቃወማለን የሚሉ ብዙ ናቸው። የዚኸ አገዛዝ መቆሚያው ያ "ሕገ-መንግሥት" እንደሆነ ይዘነጉታል መሰለኝ። አቶ መለስና አገዛዛቸው በዚኸ ሕገ-መንግሥት አሁን እያደረጉ ያሉትን እያደረጉ መቀጠል ያስችላቸዋል። በዚኸ ረገድ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ በመፀሐፋቸው ያስነበቡትን ምሁራዊ ትንተና በድጋሜ ማንበቡ ለግንዛቤ ይጠቅማል።

አንድ ሌላ ግልፅ መሆን ያለበት ለጠባብ ጎጠኛና ጎሠኛ አስተሳሰብና እምነት ወያኔ ብቸኛ ተጠያቂ እንዳልሆነና በግል ንብረትነት እንደማያዝበት ነው። ወያኔው ይዞት በተነሣው የ"እኛ እና እነሱ" የልዩነትና የክፍፍል እምነት (ርዕዮት) ስንቶች ተበክለዋል? ወያኔው ቢወገድ ያ ወያኔአዊ የልዩነትና የመከፋፈል (ጎሠኝነት) አስተሳሰብና ፍልሥፍና (የፖለቲካ እምነት) አብሮ ሊወገድ ይችላል ወይ? የሚለው ነው። ቀደም ሲል እንዳልኩት እኔ እንደማየው ከሆነ መርዙ በብዙ የአገሪቱ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሠራጭቷል። አወቅነውም አላወቅነው፣ እያንዳንዱ ስርጭቱ የደረሰበት እራሱ የስርጭት ምንጭና አስተላላፊ ከሆነ ውሎ አድሯል። ስለሆነም የስርጭቱ ቀዳሚ ባለቤት (ዓይነታው ወያኔ)

ቢፈልግ እንኳ ሊያስቆመው አይችልም። ክትባት ከራሱ ከበሽታው እንደሚሠራ ሁሉ ወያኔ (ዋናው ምንጭ) የልዩነት፣ የጎጠኝነትና የመከፋፈል በሽታን ለማጥፋት በሚደረግ ዘመቻ በክትባትነት ሊያገለግል የሚችልበት ልዩ ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ለዚኽም ነው ሥርዓቱን ከድርጅቱና ከመሪዎቹ ባለፈ መልኩ ጠበቅ አድርገን እንይ የምለው። መሪዎቹ እራሣቸው የዚኽ ሥርዓት እስረኞች ናቸው።

የሚገርመው እንቆቅልሽ ግን ይኽንን ወያኔአዊ ጎጠኝነትና ከፋፋይ አስተሳሰብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ፣ በግልፅም ይሁን በስውር በዚያው ልክ በዓይነቱ ማለት ጎሠኝነትን (ጎጠኝነትን) መሠረት ባደረገ አመለካከትና አሠላለፍ ለመዋጋት (ለመቃወም) በአንዳንድ ወገኖች የሚደረገው መኳተን ነው። ጨለማን በብርሃን እንጂ በጨለማ ለማጥፋት አይቻልም። ነገሩን ይበልጥ ትርጉም የሚያሳጣው ጥረቱ በኢትዮጵያና በአንድነት ስም መሆኑ ነው። አንዳንዶች ይኽንን ዓይነት አካሄድ ትክክለኛነት ወይም "አማራጭ-የለሽነት" ለማረጋገጥ 'መርዝን በመርዝ' ወይም 'እሾህን በሾህ' የሚሉት ፈሊጥ አላቸው። እንደኔ እንደኔ ይኽ ዓይነት አስተሳሰብ የኒኩሊየር ጥቃትን በኒኩሊየር መልሶ የማጥቃት እርምጃ ለመመለስ የሚደረግ የዋህ ስሌት ነው። የዋህ የሚያሰኘውም ውጤቱ ተያይዞ መጥፋትን ማረጋገጥ ብቻ ስለሆነ ነው። እዚኽ ላይ ነው እንግዲኽ በተቃዋሚው ክፍል ያለው አንዱ ችግር።

ወያኔ ድርጅቱ አገራዊ የመንግሥት ሥልጣንን ቢጨብጥም ቅሉ ድርጅቱ በመሠረቱ ለቆመባቸው መርኅዎች ተገዥ ከመሆንና ከዚኽ ፖለቲካዊ እምነት የመነጨ መተክሎችን መከተልና እነዚኽንም ማስፈፀም ዋና ፖሊሲው አድርጎ ሊይዝ እንደሚችል በግልፅ መታወቅ ይኖርበታል። እነዚያ ፖለቲካዊ እምነቶችም ድርጅቱ ለሚያራምደው የአገዛዝ ሥርዓት ዋነኛ የመኖር ምክንያትና የኀልውና መሠረት እንደሚሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ቀደም-ሲል እንደተጠቀሰውም አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የሕወሓት ወያኔአዊ አገዛዝ የአገሪቱን ሁለንተናዊ ሕይዎት ቀፍድዶ እንደያዘ የአደባባይ ምሥጢር ነው። በሥልጣን ላይ እስከቆየ ድረስም ይዞታውን እያጠበቀና እያጠናከረ እንጂ ተቃራኒው ሊሆን አይችልም። ብዙ ወገኖች ድርጅቱ ለዚኽ የበቃበትን ምክንያት ትግሬ ስለሆኑ ነው ከሚለው ግልብ አመለካከት ጀምሮ እስከ ድርጅታዊ ጥንካሬ፣ ከዓለም-አቀፍ ሴራ እስከ ሌላው ኢትዮጵያዊ ድክመት፣ ወዘተ... እንደሆነ አድርገው በልዩ ልዩ መንገድ ይገልፁታል። እንደኔ እንደኔ ይኽ ድርጅት ላለበት ይዞታ የበቃበት መሠረታዊ ምክንያት ከምንም በላይ ይዞት ከተነሣው የ"እነሱና እኛ" የእምነት ፍልሥፍና (ርእዮት) የመነጨውና በሱም ላይ መሠረቱን የጣለው አደረጃጀቱ ነው። ይኽ ማለትም በአጭሩ በጠባብ ፖለቲካዊ ጎጠኝነት ላይ መሠረቱን የጣለና የግድ ሌላውን በጠላትነት ያስሠለፈ እምነት (ርዕዮት) ዙሪያ የተቀነቀነ ፍልሥፍና እና ይኽን የፖለቲካ እምነት በተግባር ለመተርጎም የተከተለው "ዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት" በሚል የሚታወቀው ከዴሞክራሲ ጋር ትውውቅ የሌለው እክራሪ "ግራ-ቀመስ" አረደረጃጀት ነው።

ይኽ ድርጅት ከሥር-መሠረቱ ጀምሮ ኀልውናው በዚኽ ፍልሥፍናና አደረጃጀት ላይ የተመሠረተ በመሆኑም ጅምሩ ላይ እንደወጠነው "የትግራይ ሪፓብሊክ" አቋቁሞ በትግራይ ይወሰን ወይም በኋላ በታሪክ አጋጣሚ አጠቃላይ በአገር ደረጃ ሥልጣን ይያዝ የእምነት፣ የአመለካከትም ይሁን የአሠራር ለውጥ ሊያመጣም ይሁን ሊኖረው አይችልም። ድርጅታዊ ተፈጥሮው (ፍልሥፍናው) ስለማይፈቅድለት! ይኽ ድርጅት በዚኽ ፍልሥፍናውና አደረጃጀቱ አማካይነት ኀልውናውን በሦስት ማዕዘን ተጠላላፊና ተደጋጋፊ ምሰሶዎች ላይ ማሣረፍና ማቆም ችሏል። እነሱም፣ ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ናቸው። የነዚኽን ማዕዘኖች ዝምድናና የማይነጣጠል ትሥሥር በደንብ ያጤኗል።

የአረመኔነቱ ውልድ በሆነው ሁለ-ገብ ድክመቱ፣ ብቃተ-ቢስ አመራሩና ይዞታው ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፉን የነሣው ከንቱው ደርግ ሲንኮታኮት በአገሪቱ የተከሰተውን የፖለቲካ ክፍተት በተገቢ የተጠቀመበት ይኽ ድርጅት (ወያኔ)፣ በጠብ-መንጃ

(በጉልበት) የፖለቲካ ሥልጣንን ጨበጠ፣ በኃይል የጨበጠውን (የያዘውን) የፖለቲካ ሥልጣን ተጠቅሞ "ዓብዮታዊ ዴሞክራሲ"ን የአገዛዙ ፍልሥፍና መርኅ በማድረግ አጠቃላይ ሥልጣንና የአገሪቱን ሃብት አግበስብሶ በመያዝ የኤኮኖሚ ኃይሉን ማጠናከር ቻለ፡፡ እያንዳንዱን በአጭሩ እንይ፡፡

በወታደራዊ መስኩ የደኅንነትና የፀጥታው መዋቅሮች ጭምር በአገዛዙ መረብ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ናቸው፡፡ በወታደራዊ-ደኅንነት-ፀጥታ መዋቅሮች በቀናዒነት የሚቆጣጠረው የፖለቲካው መስክም አጠቃላይ መንግሥታዊና ቢሮክራሲያዊ ክፍሉን እንዲሁ ከላይ እስከታች በሙሉ ቁጥጥሩ ሥር እንዲያደርግ አስችሎታል፡፡ በተለይ ለዚኽ ደግሞ "ሕገ-መንግሥታዊ" ሽፋን የተሰጠው በመብት ስም በቀቢፀ-ተስፋ ለሚነሆልሉ መገንጠልን የሚፈቅድና ዜጎች ተለያይተው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ቋንቋን መሠረት ባደረገ ኅሠኛና ኅጠኛ መንግሥታዊ አወቃቀርና አደረጃጀት በትኖ እርስ በርሱና እያንዳንዱ በውስጡ እራሱን እንዲበላ፣ እንዲተራመስ፣ ሕዝብ እንደ አንድ አገር ሕዝብ ብሔራዊ ዕይታ እንዳይኖረውና ለጋራ ጥቅሙ በጋራ እንዳይቆም የሚያደርግ በታኝ የፖለቲካ አሠላለፍን አስፍኗል፡፡ በዚኽ ሙሉ ቁጥጥሩ ሥር ባለ የፖለቲካ አቅሙ አማካይነት ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የአገሪቱን የኤኮኖሚ ዘርፍ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሯል፡፡ በዚኽም የማን-አለብኝ እብሪታዊ የባለቤትነት ስሜትና መንፈስ በአገሪቱ ሃብት ላይ ባለው ሙሉ ቁጥጥር የአገርን ዳር ድንበር ሳይቀር እንደፈለገውና ከኪስ ወጥቶ እንደሚሰጥ የግል ገንዘብ ለባዕዳን አሣልፎ መስጠት ድረስና ከቅርብ ጊዜ ወዲኽ ደግሞ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የአገሪቱ ዜጎች በጠኔ እየተሰቃዩና ለአሳፋሪ ምግብ ምፅዎታ የዓለም-አቀፍ ኅብረተሰብ እንዲረባረብ እየተጠየቀ፣ ዜጎች የሚያርሱት ማሣ ተነፍጓቸው ቤታቸውን ዘግተው፣ ቀያቸውን ለቀው ለልመና እየተዳረጉ ባሉበት ሁኔታ፣ ደኖች እየተመነጠሩ ጭምር የአገሪቱን ድንግልና ለም የእርሻ መሬቶች ለባዕዳን በሃራጅ እስከ መቸብቸብ ደርሷል፡፡ (በዚኽ ጉዳይ ላይ በተለዬ ያቀረብኩትን አስተያየት ይመለከቷል)፡፡

ይኽንን በሦስት ማዕዘን ቁልፍልፍና ተደጋጋፊ ትሥሥር ላይ የተዋቀረውን የአገዛዙን ይዞታ በቅጡ ካለመረዳት ይመስላል አዲስ ነው ባይባልም አንዳንድ ወገኖች ከቅርብ ጊዜ ወዲኽ ሲያቀነቅኑት የሚደመጥ ህቶት አለ፡፡ ይኸውም "ይኽ ድርጅት በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሃብት ስላካበተና በተለይ መሪዎቹ ዕድሜአቸው እየገፋ ስለሆነ ያላቸውን ሃብት በሰላም ለመብላት ይፈልጋሉ፣ በዚኽም ምክንያት ቢያንስ ሃብታቸውን ላለማጣት ሲሉ ሁኔታዎችን ላላ ማድረግና ሥልጣንንም ቢሆን ከመጋራት ወደ-ኋላ ሊሉ አይችሉም፣ ይኽን ከማድረግ ሌላ አማራጭ የላቸውም" ይሉናል፡፡ አዎን ልክ ነው በዓለም-ደረጃ ካሉ ሃብታሞች መኻል ወደ መቆጠሩ እያቀኑ ያሉ ወያኔአዊ ሃብታሞች አቆጥቁጠዋል፡፡ ይኽ ደግሞ ከመሬት በላይም ሆነ በመሬት ከርስ ውስጥ ያለ የአገሪቱን ሁለንተናዊ ሃብት በይሉኝታ-ቢስ ስግብግብነት በግል ንብረትነት የተቆጣጠረ ድርጅት ባለቤቶች (መሪዎች) የናጠጡ ሃብታሞች መሆናቸው ሊገርም ከቶ አይገባም፡፡ አጠያያቂው ጉዳይ እሱ አይደለም፡፡

ጥያቄው ይኽ ድርጅት ከላይ ከተጠቀሱት ኅልውናውን ከጣለባቸው ሦስት ማዕዘናት ውስጥ (ከተቀመጠበት ባለ ሦስት እግር የሥልጣን ወንበር ላይ) አንዱንም መልቀቅ (ማጣት) እንደማይችል መረዳት አለመቻላችን ነው፡፡ የአንዱ መዛባት አጠቃላይ የጨዋታ ሕጉን ያበላሽበታል፡፡ ምክንያቱም ያን ማድረግ ማለት ኅልውናውን ማናጋት፣ እሱነቱን ማጣት ወይም አዲስ ተፈጥሮን መያዝ ሊሆን ነው፡፡ ታዲያ ከድርጅቱ ፍልሥፍናና ከፍልሥፍናው አቀንቃኞች (ከመሪዎቹ) ይኽ ሊጠበቅ ይችላል? እዚኽ ላይ በእርግጥ አንድ የሚነሣ ክርክር አለ፤ ይኸውም "ዞሮ ዞሮ የዚኽ ድርጅት መሪዎች ሰዎች ናቸውና ሌላው ቢቀር ዘለዓለም ሊኖሩ ተፈጥሮ አይፈድላቸውም" የሚል፡፡ አዎን የተፈጥሮ ሂደትማ አያጠያይቅም፤ መታየት ያለበት ግን በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የዚኽ ድርጅት መሪዎች በያዙትና በሚያራምዱት ዓይነት ጠባብና ፍፁም አምባ-ገነን ፍልሥፍና የሚመሩ ሁሉ ይኽን እውነታ ተቀብለው ከአይቀሬው ውድቀታቸው ወይም ኅልፈታቸው በፊት አዲስ አቅጣጫን በፍላጎታቸው ሲመርጡም ሆነ ሲይዙ የታየበት ጊዜ የለም፡፡ ለመሆኑ የትኛው የማፍያ

ወይም የአደንዛዥ ዕፅ ነጋዴ (ድረግ ካርቴል) ድርጅትና መሪ ነው 'አሁንስ በቂ ሃብት አጠራቅሜአለሁና ይብቃኝ' ብሎ ሥራውን በፈቃዱ የተወ? የትኛውስ አምባ-ገነን አገዛዝ ነው በበጎ ፈቃዱ ሥልጣኑን ያስረከበ? ያውም በሦስት-ማዕዘን ውቅር የጎልውና መሠረቱን ያበጀ ኃይል?! ሦስቱም ማዕዘናት እኩል ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው:: የአንደኛው መዳከም ሌሎቹን ሁለቱን ያዳክማል አልፎም በሁለቱም ላይ ያለውን ቁጥጥር ያሳጣዋል:: የፖለቲካ ቁጥጥሩን ካጣ በሱ (በፖለቲካው) የበላይነት አማካይነት እንደፈለገው የሚቆጣጠረውን የኤኮኖሚ ዘርፍ መቆጣጠር አይችልም፣ የኤኮኖሚ ዘርፉ ከሙሉ ቁጥጥሩ ውጭ ቀርቶ ከተዳከመ ደግሞ በወታደሩና በፀጥታው በኩል ያለውን ቁጥጥር ያሣጣዋል፤ ይኸ አዙሪት መልሶ ይገጥማል:: ይኸ ዑደት ካልቀጠለ ደግሞ አድራጊ-ፈጣሪ የሆነ ድርጅታዊ ጎልውና ያከትማል::

ስለሆነም አንድ ሁለት ሰው በተቃዋሚው ስም ቤተ-መንግሥት ገብቶ ከአገዛዙ ቁንጮ ጋር ግብር ስለበላ፣ ነገ በተግባር ቅንጣት ተፈፃሚነት የማይኖረው "ቃል" ስለተገባ በፀፀት የማይመለስ ስህተት ውስጥ ያስገባ አገዛዙ የፈለገውን በፈለገው መልክ ያዘጋጀው ሰነድ ስለተፈረመ፣ "ያው ወያኔ ተሸንፏል፣ እየተንበረከከ ነው፣ ወዘተ…" ማለት ትርጉም-የለሽ ነው:: ይኸ በጭንቅላቱ የቆመ፣ የነሆለለና ጨርሶ የዞረበት፣ ፈፅሞ የዚኸን አገዛዝ ማንነትና ምንነት ትንሽም እንኳ ካለመረዳት የመነጨ አስተሳሰብ መደመጡ በውነት የሚገርምም የሚያሣዝንም ነው::

አምባ-ገነኖች ሥልጣንን እስከ ዕለተ-ኅልፈታቸው የሙጥኝ የሚሉት ከሥልጣንና በሱም የሚገኝ ጥቅማ-ጥቅምን ላለማጣት ብቻ አይደለም:: አንዱና ዋናው ምክንያት አገዛዛቸው በተነከረበት ሰብዓዊ መብት ገፈፋ፣ ግፍ፣ ግድያ፣ ወዘተ … መጠየቅን ስለሚፈሩ ነው:: ቀደም-ሲል ለመግለፅ እንደሞከርኩት በወያኔ ዓይነት ፍልሥፍና የሚመሩ ድርጅት መሪዎች ገና ሀ ብለው ትግል ሲጀምሩ አንስቶ በ"ትግሉ/አብዮቱ" ስም እጃቸው ብዙ ወንጀሎች ውስጥ ስለተዘፈቀ አንዴ በመሪነት ቦታ ላይ ከተቀመጡ ከዚያ ቦታ ሕይዎታቸው እስከሚያልፍ የማይለቁት ከተጠያቂነት ማምለጥ ስለማይችሉ ነው፣ መሄጃ የላቸውም::

አሁንም ግልፅ እንሁን በአገራችን ያለው ሁኔታ እንዲቀየር የፈለገ ሁሉ በአገዛዙ በጎ-ፈቃድና ፍላጎት ብቻ የሚመጣ ለውጥ እንደማይኖርና ሦስቱንም የአገዛዙ የጎልውና መሠረት የሆኑ ማዕዘናት አንድ ላይ ሊዳሰስና ሊመለከት በሚቻልበት አጠቃላይ ሂደት እንጂ በቁንፅል የሚሆን እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል:: ለዚኸም ነው ብዙዎቻችን በአገራችን መምጣት የሚኖርበት ለውጥ መሠረታዊና ይኸም ዘለቄታዊነት እንዲኖረውና ሰላማዊ እንዲሆን ከተፈለገ በሰከነ ብሔራዊ እርቅ ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል የምንለው:: ይኸ ደግሞ ገዥውን ድርጅት የጨመረና ማንንም ያላገለለ ሊሆን ይገባል:: ያ ደግሞ በተራው ከአጉል ምኞት የተላቀቀና በቀቢፀ-ተስፋ ከሚዋዥቅ አመለካከት የጠራ፣ መሠረታዊ የሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ የአንድነት የለውጥ ኃይል መኖርን የግድ ይላል:: ችግራችንም እዚኸ ላይ ነው:: እነኝኸን ጥያቄዎች በጥንቃቄ ሳያጠኑ፣ ሳይመረምሩና ሳያጤኑ አንድን ሁኔታ ለመቀየር የሚደረግ ትግል ውጤት-አልባና አድካሚ የዳበሣ ጉዞ ከመሆን አልፎ እንዲያውም እንዲለወጥ ለሚፈለገው ክፍል ያልታሰበ አጋዥና ዕድሜ-ቀጥል ሊሆን ይችላል:: ከዚኸ አንፃር በአገራችን ያለውን አሉታዊ ሁኔታ ለመቀየር የሚታገለው ክፍል ምን ያኸል ለአገዛዙ ዕድሜ መራዘም አስተዋፅዖ እያደረገ እንዳለ በጥሞና የተጤነ አይመስለኝም::

ሁሉም እንዲመልስ የሚያስፈልገው ጥያቄ፣ ይኸ ድርጅት በአሥራ-ሰባት ዓመት ትግሉ ጊዜ ላደርግም ያለውን አድርጓል ወይ? ታዲያ ምን አምጣ ነው የምንለው? የሚሠራው ያመነበትን፣ ጥቅሜን ያስጠብቅልኛል ያለውንና የታገለበትን አይደለም? ጥያቄው የግርንቢጥ ይሁን ካልተባለ በስተቀር መሆን ያለበት ለምን ይቀየር? የሚለው ይመስለኛል::
ይኸ ደግሞ የሥርዓቱ አራማጆች በታሪክ አጋጣሚ ከትግራይ ስለተወለዱ ፈፅሞ አይደለም:: ቁም-ነገሩ ከየት መጡ ከየት ሣይሆን የያዙትና የሚከተሉት ፍልሥፍና (ርዕዮት) ላይ ነው::

አሁን ይኽ ድርጅት የሚያደርገውን ማንም በሱ ፍልሥፍና የሚመራ “ነፃ-አውጭ” ድርጅት ሁሉ በሱ ቦታ ቢሆን የሚያደርገው ነው። ይኽንን ነጥብ ነው በተለይ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፈው የአንድነት ኃይል የማያጤነው። ስለዚኽ ኢትዮጵያውያን መገንዘብ የሚኖርብን ትኩረታችን የመከፋፈልና የልዩነት ሥርዓት አራማጆች ላይ በቁንፅል ሣይሆን እራሱ እምነቱ (ርዕዮቱ) ላይ መሆን ይኖርበታል።

እንግዲኽ በፖለቲካው መስክ የተሠለፈ ሁሉ እራሱን ይመርምር። አገዛዙን መቃወም ብቻ ፈጽሞ በቂ አይደለም። መቸም ፖለቲካው በጭንቅላቱ ስለቆመ በአሁኑ ጊዜ አገዛዙን ማውገዝ ብቻ እንደ ፖለቲከኛ የሚያስቆጥርበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። (አንድ ግለሰብ ወያኔ ሥልጣን ሲይዝ ሚኒስትር እንዲያደርጉት አማላጅ ልኮ ደጅ ቢጠናም ወያኔ ልመናውን ችላ ስላለው ሁልጊዜ በየንግግሩ ወያኔ፣ ወያኔ ማለት ስለሚያዘወትር እንዲያውም የድርጅት ም/ሊቀ-መንበር ሆኖ እንደነበር አስታውሳለሁ)። ማንኛውም ተቃውሞ በእምነት (በመተክል) ላይ ሲመሠረት መልክ አለው፣ የምንቃወመውንም ክፍል መቃወም የሚኖርብን የምንቃወመው ክፍል በያዘው ፍልሥፍናና ያ ፍልሥፍና በአገርና በሕዝብ ላይ በሚያሳድረው (በሚያደርሰው) አሉታዊ ገፅታ እንጂ በፍልሥፍናው አራማጅ ማንነት (የትውልድ ቦታም) ሆነ የግል ጥቅማችን ስለተነካ ብቻ ያንን አገራዊና ሕዝባዊ ሽፋን ለመስጠት በመሞከር ፈፅሞ ሊሆን አይገባም የሚል እምነት አለኝ። ተቃውሞ መተክላዊ የሚባለው፣ አጥጋቢ የሚሆነውና ተቀባይነት የሚኖረው በግል ቂምም ሆነ በግል ጥቅም ምክንያት የሚነሣ ሣይሆን ከራስ በላይ በሆነ በአገርና በሕዝብ ክቡር ጉዳይ ላይ ሲመሠረት ብቻ ነው።

ስለሆነም በእኔ እምነት አቋማችን፣ በተለይም አገርንና ሕዝብን በሚያክል የፖለቲካ ጉዳይ፣ መመሥረት ያለበት በምንጠላው (በምንቃወመው) ላይ ሣይሆን በምንደግፈውና በምንፈልገው ላይ መሆን ይኖርበታል። ምክንያቱም ትግላችን እንዲኖር በምንፈልገው ላይ ከሆነ ዕይታችን አይጠብም። ትግላችን በምንጠላው (ድርጅትም ሆነ ግለሰብ) ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ከሆነ ግን ትኩረታችን ሁሉ በዚያ ክፍል ላይ ይሆንና፣ መልእክቱን ሣይሆን መልእክተኛውን እንዲሉ፣ ዋናውን መንሥዔና አስኳል ችግሩን መዘንጋትን ያስከትላል። የአጀንዳ ነጥባችንም ከመጥበቡ በተጨማሪ ቅድሚያን ለምንቃወመው የለቀቀና እኛን ሁል-ጊዜ በጎሉፋዊ የተከላካይነት ትግል ላይ እንድንጠመድ ያደርጋል።

ትግላችን ለአገራዊ አንድነትና ለሕዝብ ሁለንተናዊ መብቶች መከበር እስከሆነ ድረስ የኃይል አሰላለፋችንን አጥርተን ለመለየት ያስችለናል። ያንን ማድረግ ደግሞ ትግላችን ፈር ሳይለቅ በማንም ይቀንቀን በማ በነዚያ እውን እንዲሆኑ በንፈልጋቸው መሠረታዊ አገራዊና ሕዝባዊ እምነቶችና እሴቶች እውን መሆን ላይ እንቅፋት የሆኑ አስተሳሰቦችና ፍልሥፍናዎች ላይ ሊሆንና አቅማችንንና ጉልበታችንን ሳናባክን አስተባብረን ለአስተማማኝ ውጤት መብቃት ያስችለናል። አጠቃላይ የትግሉ ልዕለ-ግብ ላይ ማተኮርና ከአገራችንና ከሕዝባችን መሠረታዊ ጥቅሞችና ከዘለቄታው ግባችን ጋር ምንም ግንኙነት በሌለው፣ ሌሎቻችን በማያገባንና በማይመለከተን፣ በራሱ ልዩ ልዩ ምክንያት ለጊዜው ወያኔን ጠላሁ ከሚለው ጋር ሁሉ ሳንነሆልልና ጊዜ ሳይባክን ሕዝባችንን የሥልጣኑ ባለቤት ማድረግ ይጠበቅብናል። ትግላችን ለአገርና ለሕዝብ እስከሆነ ድረስ ለአገራዊ አንድነትና ለሕዝባዊ መብቶች መከበር እንቅፋት ከሆኑ አስተሳሰቦችና ፍልሥፍና አቀንቃኞች ጋር ሁሉ መሆን ይኖርበታል። በአንድ መልኩ ይሁን በሌላ አገዛዙ የሚከተላቸውን መርኅዎች የሚከተል፣ የሱ ፍልሥፍና የተጠናወተውም ይሁን በልዩ ልዩ ሰበብ-አስባብ በጋራ ትግሉ ላይ ደንቃራ የሚሆን ሁሉ የአገዛዙን ዕድሜ እንዳራዘመና በዚያም ምክንያት የሕዝባችን ሰቆቃ እንዲቀጥል እንዳገዘ ስለሚቆጠር ወያኔ ነው።

ስለሆነም ኢትዮጵያውያን አብሮ፣ ተባብሮና ተከባብሮ፣ ተደጋግፎና ተሳስቦ፣ በእኩልነት በጋራ ለመኖርና በሁሉም ረገድ በጋራ ለመበልፀግ የመጀመሪያው እርምጃችን ይኽንን ሃቅ መረዳትና ቀጥሎም ይኽንን ኋላ-ቀር የልዩነት አጥር ማፍረስ ይሆናል። የልዩነት አጥርን

ለማፍረስ ግን የልዩነት አጥር አጣሪዎችን አቅፎ የሚሆን ጉዳይ አይደለም:: የልዩነት አጥር ያጠርን ሁሉ ኅብረተሰባችን ለሚገኝበት ሁኔታ አስተዋፅዖ እንዳደረግን፣ ያም በወደፊት በጎ እርምጃችንና የጋራ ተስፋችን ላይ ያለውን እንቅፋትነት መገንዘብና ስህተትነቱን በድፍረት ማመንና መቀበል ያስፈልጋል:: ያም በቂ አደለም ያጠርነውን የልዩነት አጥር አብረን ለማፍረስ በቅንንነትና በቁርጠኝነት በተግባር መሠማራት ያስፈልጋል:: (በቅርቡ ዶ/ር ነጋሦ ጊዳዳና አቶ ስዬ አብርሃ የወሰዱት አቋም ለዚኽ እርምጃ ምሣሌኣዊ የሚሆን፣ በጎና እሰየው የሚያሰኝ ነው)::

ይኽንን የተዛመተ በሽታ እራሣችን በሽተኛ ሆነን ሣይሆን ጤነኞች ሆነን፣ ከዚኽ በሽታ ነፃ ሆነን በጤናማ አስተሳሰብ ብቻ ነው ልናስወግደው የምንችለው:: በሽታው ከዚኽ አገዛዝ ውጭ ፈልቷል፣ ተዛምቷልና ያለውን አገዛዝ በማስወገድ ብቻ ጤና አይገኝም:: ስታሊን ስለተወገደ ስታሊናዊ አስተሳሰብ አልተወገደም፣ ሊወገድም አይችልም:: እንኳን የመለስ ዜናዊና የተወሰኑ ግለሰቦች፣ የድርጅቱ መኖር አለመኖርም እንዲሁ ወያኔኣዊ ሥርዓትን አያስወግደውም::

ትግሉ መስመር እንዲይዝ በቅድሚያ እራስን መርምሮ ከራስ ጋር መታረቅ ያስፈልጋል:: ትግሉ አሁን እንደሚታየውና እንደ ልማድ የተያዘውን በቅርብ ካለው ትላንት በአንድ ድርጅት ውስጥ አብሮን ሲታገል ከነበረውም ይሁን በሌላ መልክ ከእኛ ጎን ተሰልፎ በአገራችን ላይ ለውጥ እንዲመጣ ከሚታገል ጋር መሆን የለበትም:: እነ አቶ መለስ እንዲያደርጉ የምንጠይቀውን ስህተትን የመቀበል፣ ይቅርታ የመጠየቅና የማድረግ፣ ሕግን የማክበር፣ ለፍትኅ የመቆም፣ ልዩነትን የማክበር፣ የመቻቻል፣ የመደማመጥ ባኅሪያትን በቅድሚያ እኛው በአገራችን ላይ ለውጥ ያስፈልጋል የምንል ወገኖች ልናውቃቸውና ልንለምዳቸው፣ በተግባር ልናሳያቸውም ይገባል::

የአንዱ ኢትዮጵያዊ ጉዳት የሁላችን መሆኑን መገንዘብና በችግር ጊዜ አብሮ መቆም ያስፈልጋል:: የአንዱ መጠቀም በሌላው ኪሣራ ብቻ እንደሚመጣ የገበያ ሽቀጥ አቅልለን አንየው:: አንድነቷ በተከበረ አገራችን የዴሞክራሲያዊና ፍትኃዊ ሥርዓት እውን ቢሆን ሁሉም (ገዥም ተገዥም) ተጠቃሚ ነው:: አቶ ፀጋዬ ገ/መድኅን ሆነ አቶ አበራ የማነአብም፣ ወ/ት ብርቱካን ወይም ሌላ ማንም ኢትዮጵያዊ በግፍ ሲታሰር የእነዚኽ ወገኖች ጉዳይ አባል ለየሆኑበት ድርጅት በግል የሚተው አይደለም:: እነዚኽ ወገኖች የተነፈጉት ፍትኅ በሁላችን ላይ የደረሰ የፍትኅ መነፈግ ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል:: ወያኔ አስቦት ይሁን አይሁን እነዚኽንና ሌሎች ሥፍር-ቁጥር የሌላቸው ወገኖችን ሲያስር አባል የሆኑባቸውን ድርጅቶች ለማጥቃት ከሆነም ስህተት ነው:: ሊያውቁት የሚገባው ነገር እንኳን በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፈን ኢትዮጵያዊ የራሱ ድርጅት አባልም እንኳ ቢሆን ፍትኅ በጎደለው መንገድ ሲያስር ጥቃቱ በሁላችንም ላይ እንደሆነ ነው:: አገዛዙ እነዚኽን ሲያስር የተፈታተነው ግለሰቦቹን ብቻ ሣይሆን ሁላችንንም መሆኑ ሊታወቅ ይገባል::

አገራችንንና ሕዝባችንን ከቀጣይ ውስብስብ ችግር ለማዳን፣ እንደ ኢትዮጵያውያን የጋራ ዕድላችን ወሳኝ እንድንሆንና የተሻለ ሥርዓት ባለቤት እንድንሆን ከተፈለገ ከፖለቲካ ኅጠኝነትና ከጠባብ አስተሳሰብ ወጥተን ዕይታችን ኢትዮጵያዊ፣ አመለካከታችን ፍትኃዊ እንዲሆን ያስፈልጋል::

ኧረ እየተስተዋለ! ወገን ነቃ!

ጥር፣ ሁለት-ሽህ-ሁለት ዓ/ም